# አዲስ ዘመን

ረቡዕ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 341 ነሐሴ 11 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





## ኢንተርፕራይዞችና ሥራ ፈጣሪዎችን ለአገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት የሚጥሉ ለማድረግ እንደሚሠራ ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**


ፎቶ- ከአርካይቭ

አቶ ደመቀ መኮንን

አዲስ አበባ፡- ኢንተርፕራይዞችና ሥራ ፈጣሪዎች ለአገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት የሚጥሉ እንዲሆኑ ለማድረግ ይሠራል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለፁ።

በ2014 በጀት ዓመት የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ኢንተርፕራይዞች፣ የዘርፉ አስፈፃሚ ተቋማት፣ ሥራ ፈጣሪዎች እና የማዕከል አገልግሎት ሰጪዎች ዕውቅና የመስጠት መርሃ ግብር በትናንትናው ዕለት ተከናውኗል።

የሁለተኛው ብሔራዊ የሥራ ጉባዔ መዝጊያ መርሃ ግብር ትናንት ሲካሄድ አቶ ደመቀ ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ በሥራ ፈጠራ ፕሮግራም በክሂሎት የበቃ የተፍታታና አምራች የሆነ ትውልድን ለመገንባት እየተሠራ ነው።

ሥራ የመፍጠርና የመለወጥ አቅሙን ያሟላ ዜጋ እያበቃን፤ የሥራ ፈጠራና ተያያዥ ጉዳዮችን ማስፋፋት፣ ማጎልበትና ማሳደግ ይገባል ያሉት አቶ ደመቀ፤ ከዚህ አንፃር ኢንተርፕራይዞችና ሥራ ፈጣሪዎች የአገሪቱን ኢኮኖሚ መሠረት የሚጥሉ እንዲሆኑ ይሠራል ብለዋል።

አቶ ደመቀ፤ የሥራና ክህሎት ዘርፍ ለሌሎች የአገሪቱ ልማቶች አቅም የሚመግብ፤ ጠንካራ የኢኮኖሚ መሠረት የሚጥል እና የታፈረችና የተከበረች ኢትዮጵያን መፍጠር የሚችል መሆኑን ጠቁመው፤ ዘርፉ ከምንም በላይ ኢኮኖሚያዊ አቅም መገንባት የሚያስችል ትልቅ መሠረት መሆኑን አንስተዋል።

የላቀ አፈፃፀም ያሳዩ ኢንተርፕራይዞችና አስፈፃሚ ተቋማት፣ ሥራ ፈጣሪዎችና የማዕከል አገልግሎት ሰጪዎች የኢኮኖሚውን መሠረት ሊጥሉ መበርታት እንደሚገባቸው የጠቆሙት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የተሸላሚዎች መሪነትና ተዋናይነት ለሕዝቡና ለመንግሥት ትልቅ ፈለግና ኩራት ስለሆነ ከጀርባችሁ ፈለጋችሁን የሚከተሉ እንዲበረክቱ አድርጉ ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የሥራና የክህሎት ዘርፉ የግለሰቦችን የሥራ

ኢንተርፕራይዞችና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## «የትምህርት ጥራት ሥራ በባለስልጣኑ ብቻ የሚረጋገጥ ሳይሆን የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው»

-ዶክተር አንዷለም አድማሴ
የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ዋና ዳሬክተር

**ሞገስ ተስፋ**


ፎቶ - በኢዮብ ተፈራ

አዲስ አበባ፡- የትምህርት ጥራት ሥራ በባለስልጣኑ ብቻ የሚረጋገጥ ሳይሆን የባለድርሻ አካላትን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ተግባር ነው ሲሉ የትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አንዷለም አድማሴ ገለጹ።

የትምህርትና ጥራት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አንዷለም አድማሴ ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደገለጹት፤ ለ27 አመታት በትምህርት ላይ በተሠራው ሸፍጥ አንድ ትውልድ እንዲሰነጠቅ በመደረጉ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሥራ የሚጠይቅ ሆኗል።

እንደ ዶክተር አንዷለም ገለጻ፤ መንግሥት ለትምህርት ዘርፉ በሰጠው ትኩረት የቀድሞ የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ ሲባል የነበረው ተቋም በአዋጅ እንዲሻሻል ተደርጓል። ይህም ከቅድመ መደበኛ እስከ 12ኛ ክፍል፣ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና፣ የመንግሥትና የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በተናበበና በተቀናጀ

«የትምህርት ጥራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## የአስተዳደር ወሰኑን የማካለሉ ሥራ የሕዝቦችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ከስምምነት ተደረሰ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባና በፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የአስተዳደር ወሰኑን የማካለሉ ሥራ የሕዝቦችን ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ መልኩ ተግባራዊ ለማድረግ ስምምነት ላይ መደረሱን የሁለቱ አስተዳደር አመራሮችና የሕዝብ ተወካዮች ገለጹ።

በአዲስ አበባ ከተማና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የአስተዳደር ወሰን ማካለል ላይ በሁለቱ ወገኖች የተደረሰ ስምምነት ላይ በትናንትናው ዕለት ሕዝባዊ ውይይት ተካሂዷል።

በውይይት መድረኩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ እና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳን ጨምሮ የፌዴራልና የክልል ከፍተኛ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

በተጨማሪ ከአዲስ አበባ ከተማና የፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን የተውጣጡ የኅብረተሰብ ክፍሎች፣

የአስተዳደር ወሰኑን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




**ማህበሩ ኢትዮጵያውያን ከልዩነቶቻቸው ይልቅ ለአንድነታቸው አጽንኦት እንዲሰጡ አሳሰበ**

ገጽ 4



አቶ ንጉሱ ጥላሁን

## ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለሥራ ዕድል ፈጠራ የጎላ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑ ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በማስፋፋት ለሥራ ዕድል ፈጠራ ብሎም ሀብት ለማከማቸት ከመጠቀም አንፃር መልካም እና አበረታች ጅምሮች መታየታቸውን የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር አስታወቀ። ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የሥራ ዕድል ፈጠራን እያገዙ እንደሆነም ተጠቁሟል።

ሁለተኛው ብሔራዊ የሥራ ጉባዔ «ዘላቂ ሥራ ለብሩህ ነገ» በሚል መሪ ሃሳብ ለሁለት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ ቆይቶ በትናንትናው ዕለት ተጠናቋል።

በመርሃግብሩ ላይ በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ፣ የሥራ ስምሪትና ገበያ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን ባደረጉት ንግግር፤ በአሁኑ ወቅት ቴክኖሎጂ ለሥራ ዕድል ፈጠራ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል።

በዘርፉ የአውትሶርሲንግ፣ ፍሪላንሲንግ፣ እና ጊግ የተባሉ የሥራ ዘርፎች እየተለመዱ መጥተዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው ዘርፎቹ ለበርካታ ወጣቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ላይ መሆናቸውንም ጠቁመዋል። የተፈጠሩ የሥራ ዕድሎችም የውጭ ምንዛሬ እያስገኙ እንደሆነም አክለው ተናግረዋል።

ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም ጋር «እንቆጳ» የተሰኘ ዲጂታል ኢንተርፕሩነርሽፕን የማስተዋወቅና የማለማመድ ሥራ በመሠራት ላይ እንደሆነ አቶ ንጉሱ ገልፀዋል። እንቆጳ ውይይት በዲጂታል መንገድ ዓለም አቀፍ ተሳታፊዎችን በማሳተፍ ሰፊ ልምድ ከማስገኘቱም በላይ ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ በማሳየት ሀብት ወደ አገሪቱ ማምጣት እና የሥራ ዕድል መፍጠር መጀመሩንም ገልፀዋል።

አቶ ንጉሱ፤ ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም፣ መርሲኮርፕ፣ ጂ.አይ.ዜድ፣ ጀነሬሽን አንሊሚትድ፣ ዩኒሴፍና የመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተለያዩ ዘርፎች የሥራ ዕድል ፈጠራን እያገዙ መሆናቸውንም ገልፀዋል።

በሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር አቀናጅነት ማስተር ካርድ ፋውንዴሽን፣ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም፣ መርሲኮርፕ፣ ጂ.አይ.ዜድ፣ ጀነሬሽን አንሊሚትድ እና ዩኒሴፍ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች «ብሩህ» ተብሎ በተሰየመ የሥራ ዕድል ፈጠራ የገንዘብ እና የባለሙያ ድጋፍ እያደረጉ እንደሚገኙ ሚኒስትር ዴኤታው ተናግረዋል።

በብሩህ የፈጠራ ሃሳብ ውድድርም እስካሁን 800 ያህል ሃሳቦች ቀርበው 280 ያህሉ የውድድር ሃሳብ አቀራረብ ሥልጠና ወስደዋል። ከአጠቃላይም 50 ያህል አሸናፊዎች የተለዩ ሲሆን አሸናፊዎቹ ከድርጅቶቹ በተገኘ ድጋፍ 5 ሺህ የአሜሪካን ዶላር እንዲያገኙ ተደርጎ በባለሙያዎች ክትትል እየተደረገላቸው መሆኑን አብራርተዋል።

መርሲ ኮርፕስ የተሰኘ ዓለም አቀፍ ድርጅት ብሩህ ሱማሌ የፈጠራ ሃሳብ ውድድርን በተሳካ ሁኔታ አካሂዶ ብሩህ አፋር በሚል መጠሪያ በአፋር ክልል እያካሄደ ይገኛል። በጥቅሉ በሃሳብ አወዳድሮ መነሻ ካፒታል መስጠት ከተጀመረ ጀምሮ 3035 አመልካቾች ተወዳድረው 117 ያህል ኢንተርፕራይዞች መነሻ ካፒታል እንዲያገኙ መደረጉን ሚኒስትር ዴኤታው ገልፀዋል።

# ክልሎች ከመሬትና ከቤት አቅርቦት ጋር የተያያዙ ችግሮችን በራሳቸው እንዲፈቱ ሚኒስትሯ አሳሰቡ

**ቤዛ እሸቱ**

አዳማ፡- ክልሎች ከመሬትና መሬት አያያዝ ጋር ያሉ ክፍተቶችና ደላሎች ዋጋን የሚወስኑበት አሠራር እንዲሁም ከቤት አቅርቦት ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን በራሳቸው እንዲፈቱ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትሯ ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ አሳሰቡ።

ሚኒስትሯ ሰሞኑን የዘርፉ የ2014 እቅድ አፈጻፀም ግምገማና የ2015 እቅድ ውይይት በአዳማ ከተማ በተካሄደበት ወቅት ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ እንደገለጹት፤ ትልቅ ሀብት የሆነው መሬት እየተዳደረበት ያለው መንገድ ፍጹም ትክክል ያልሆነና መንግሥትና ሕዝብም የማይጠቀምበትና ደላሎች ዋጋን በፈለጉት መንገድ የሚወስኑበት ነው።

ይህንን ለመፍታት ክልሎች ሕገ መንግሥታዊ መብታቸውን ተጠቅመው መሬታቸውንና አካባቢያቸውን የማስተዳደር ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው ያሉት ሚኒስትሯ፤ ከተሞችና ክልሎች ኃላፊነት ወስደው መሬታቸውን ተቆጥሮ ሊታወቅ በሚያስችል መንገድ ቆጥሮ መያዝ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ከሕግ ማዕቀፍ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በማየት ድጋፍ ማድረግ የፌዴራል መንግሥት ሚና መሆኑንና በእቅድ መያዙንም ገልጸዋል።

ችግሩን ለመቅረፍ የካዳስተር የመሬት ምዝገባ ሥርዓት ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል ያሉት ወይዘሮ ጫልቱ፤ ያም ቢሆን አመራሩ በቁርጠኝነት ወስዶ ፕሮግራሙን የተገበረባቸው ቦታዎች ላይ ለውጥ እየመጣ መሆኑንና በአንጻሩ አመራሮች ችላ ያሉበት አካባቢ ላይ መሬትን ባልተገባ መንገድ እየተገለገሉበት መሆኑን ገልጸዋል። ደላሎች የመሬት ዋጋን የሚተምኑበትና የፈለጉበት የሚያደርሱበት አሠራር መቆም እንዳለበትም አመላክተዋል።

የአዳማ ከተማና የወላይታ ሶዶ ከተማ በካዳስተርና ሌጋል ሬጅስትሬሽን ሥራ እንደጥሩ ምሳሌ መውሰድ



ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

ፎቶ -ገበዑ ገብሬ

እንደሚቻልና የተሻለ አፈጻጸም ያስመዘገቡ ከተሞችን ልምድ ወደሌሎች ከተሞች በማስተላለፍ ሥራዎች ወደፊት እንዲራመዱ ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ መሠረታዊ የከተማ ነዋሪ ችግር ከቤት ጋር የሚያያዝ ነው። ሰዎች ከገቢያቸው ወደ 65 በመቶና ከዚያ በላይ ለቤት ኪራይ ወጪ እያደረጉ ይገኛሉ። የዚህ መንስኤም ቀድሞ የነበረው የቤት ስትራቴጂ በዋናነት መንግሥት በሚያቀርበው የቤት ሞዳሊቲ ላይ ብቻ ያተኮረና የቤት ባለቤትነትን ብቻ መሠረት ያደረገ እንዲሁም ሌሎች አማራጮችን የዘጋ በመሆኑ ነው።

ቀድሞ የነበረው ስትራቴጂ ክፍተት ያለበት በመሆኑ የቤት ግንባታን ከመንግሥት እጅ በማውጣት የግል ዘርፉ በስፋት የሚሳተፍበትን ሁኔታ ማመቻቸት እንደሚገባና ሁሉንም የቤት ባለቤት ማድረግ ስለማይቻል ተደራሽ የሆነ የኪራይ አማራጭን ለማስፋት ወደ እንቅስቃሴ መግባቱን ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ ካሁን በፊት በነበረው አሠራር የኮንዶሚኒየም ግንባታን የፌዴራል መንግሥት ይዞት ስለነበር አሁንም ክልሎችና የከተማ መስተዳድሮች የፌዴራል መንግሥትን የሚያዩበት ሕጋዊ ምክንያት የለም። ሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ለከተማ ነዋሪዎቻቸው የቤት ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረገ አቅርቦት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። በአስር ዓመቱ አራት ነጥብ አራት ሚሊዮን ቤቶችን በከተሞች 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ቤቶችን በገጠር ማዕከላት ለመገንባት እቅድ ተይዟል።

# ዩኒቨርሲቲዎች የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመስጠት እንዲዘጋጁ መመሪያ ተሳለፈ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ዩኒቨርሲቲዎች የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመስጠት የሚያስችላቸውን ዝግጅት እንዲያደርጉ መመሪያ መተላለፉን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመስጠት የሚያስችላቸውን ዝግጅት እንዲያደርጉ መመሪያ ተላልፏል።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የ2015 ዓ.ም የትምህርት ካላንደራቸው ከመስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የሚሰጠውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት መልቀቂያ ፈተና ታሳቢ ያደረገ መሆን እንደሚገባውም ተገልጿል።

በተጨማሪ ከመስከረም 28 - ጥቅምት 17 ቀን 2015 ዓ.ም በሁሉም የዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ ምንም ዓይነት መደበኛ ተማሪ እንዳይገኝ፣ ለፈተናዎች ማቆያ ቦታና የምግብ አቅርቦት ዝግጅት እንዲደረግም ትእዛዝ ተላልፏል።

ከፈተና ደህንነትና አቅርቦት ጋር በተያያዘ የፈተናውን አሰጣጥና ደህንነት የሚቆጣጠር በዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት የሚመራ ዋና ግብረ ኃይል እንዲሁም በየካምፓሶቹ ኃላፊ የሚመራ ንዑስ ግብረ ኃይል እንዲደራጅ መመሪያ ተላልፏል።

የ2014ዓ.ም የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከመስከረም 30 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ እንደሚሰጥ የትምህርት ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። የትምህርት ሚኒስቴር የትምህርትን ጥራትን ለማሻሻል በአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፎች ሌሎችንም የተለያዩ እርምጃዎች በመውሰድ ላይ መሆኑም የሚታወስ ነው።

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ ከዚህ ቀደም እንደገለጹት፣ የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በኦንላይን መስጠት እስከሚጀመር ድረስ በዩኒቨርሲቲዎች መሰጠቱ ይቀጥላል።

የሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና በዩኒቨርሲቲ እንዲሰጥ የተወሰነው የፈተና ስርቆትና ማጭበርበርን ለማስቀረት ታስቦ በመሆኑ ተማሪዎች ትምህርት በሥራና በታታሪነት የሚገኝ መሆኑን አውቀው በርትተው መማርና ማጥናት እንዳለባቸው ትምህርት ሚኒስቴር አሳስቧል።

# «የወሰንና የብሔር አጥር ከመግባባት ሊያግደን አይገባም»

- አቶ ግርማ የሸጥላ

በአማራ ክልል የፕሬዚዳንቱ የሕዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት አማካሪ

**አስናቀ ፀጋዬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የወሰንና የብሔር አጥር ከመግባባት ሊያግደን አይገባም ሲሉ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በምክትል ርዕስ መስተዳድር ማዕረግ የፕሬዚዳንቱ የሕዝብ ተሳትፎና አደረጃጀት አማካሪ አቶ ግርማ የሸጥላ ተናገሩ።

አቶ ግርማ ከሰሞኑ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት «የጋራ እሴቶቻችን ስለ ኢትዮጵያ» በሚል መሪ ሀሳብ በደሴ ከተማ በተዘጋጀው የፓናል ውይይት ላይ እንደተናገሩት፣ አገራዊ መግባባት የሚመጣው የአካባቢ አስተዳደሮች ሻገር ብለው መወያየት ሲችሉ ነው።

ከዚህ ባለፈ አገሪቱን ከፍ የሚያደርጓት ለአፍሪካና ለዓለም ጭምር የሚበቁ እሴቶች በመኖራቸው እነዚህን እሴቶች ኢትዮጵያን ለማሻገሪያና የገጠሟትን ችግሮች እንደመፍቻ መሣሪያ መጠቀም እንደሚገባም አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ የገጠማት ፈተናና ችግር የሆነ ቦታ ተፈጥሮ አልቆመም ያሉት አቶ ግርማ፤ ‹‹ቀስ በቀስ የቆምነውን ሰዎች የሚያደማ ዓይነት ሆኖ ብዙ እየተጎሳቆልን›› ነው ብለዋል።

‹‹ችግሩ አለ ብለን የምናምን እንደሆነ ብናውቅም ችግሩን ለመፍታት ለምን ፍቃደኛ አልሆንም? ለምንስ ይህን እውነት ተቀብለን መሥራት አልቻልንም?›› የሚለው መሠረታዊ ጥያቄ መሆኑንም አቶ ግርማ ተናግረዋል።

ችግሮቹን ለመፍታት አንችልም እንዳንል ችለን ያለፍናቸውና የፈታናቸው በርካታ ዓለምን ያስደነቁና ያስገረሙ ሁነቶች አሉ ሲሉም ተናግረው፤ ከምንም በላይ ነፃነትን ላለመስጠት መሞትና መስዋትነት መክፈል ችግሮችን የመፍታት አቅማችን እስከምን ያህል ድረስ እንደሆነ ማሳያ መሆኑን ገልፀዋል።

በመሰዋትነት የመጣውን ነፃነት እርስበርስ ለመጋደልና ለመጣላት የምንፈልገው ከሆነ ግን ጉዳዩን ሰክነና እውነቱን ተጋፍጦ በችግሩ ዙሪያ መወያየትና መነጋገር እንደሚጠይቅ አቶ ግርማ የሺጥላ ጠቁመዋል። አገሪቱን እየገጠሙ ባሉ ችግሮች ዙሪያ ሁሉም ዜጋ ኃላፊነት እንዳለበትም አስምረዋል።



ይህን ኃላፊነት ለመወጣት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ወደጥፋት መንገድ የሚገፉ ምክንያቶች መኖራቸውንና እነዚህ ምክንያቶች ኢትዮጵያ እያሸነፈች ወደፊት ከመሻገር እንደማያግዷትም አቶ ግርማ ጠቅሰዋል።

ኢትዮጵያ ባሸነፈችበት ቦታ ላይ ሆነን ስንነጋገር ለአዲስ አሸናፊነት በሚገባ መሥራት አለብን ብለው፤ ይህ አሸናፊነት የሚጀምረው በቅድሚያ አካባቢ፣ ቤተሰብና ግለሰብ ራሳቸውን ማሸነፍ ሲችሉ መሆኑን ገልፀዋል። ለዚህም ሁሉም በኢትዮጵያ የትኛውም አካባቢ የሚገኝ ማህበረሰብ በአካባቢያዊ ጉዳዮች መመካከርና ኢትዮጵያን ለማስቀጠል መወያየት እንደሚገባው አሳስበዋል።

ከዚህ አንፃር አገራዊ የምክክር መድረኩ አካባቢያዊ የምክክር መድረክ እንደሚያስፈልገውም ጠቅሰዋል። በዚያው ልክ ወሰን ተሻጋሪ ንግግር እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

# በመዲናዋ ከ2016 የትምህርት ዘመን ጀምሮ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ እንደሚሆን ተገለጸ

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በ2016 ዓ.ም ጀምሮ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንደሚሆን የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። በመጪው የትምህርት ዘመን በአዲስ አበባ ትምህርት የሚሰጠው በአዲሱና በነባሩ ሥርዓተ ትምህርት መሆኑ ተነግሯል። በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት መጽሐፍትና መመሪያዎች በአማርኛና በአፋን ኦሮሞ መዘጋጀታቸውም ተጠቁሟል።

የአዲስ አበባ የትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ቁጥጥር ባለሥልጣንና የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ላይ ትናንት ከባለድርሻ አካላት ጋር ምክክር ባደረጉበት ወቅት የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ እንደተናገሩት፣ በመዲናዋ ከ2016 የትምህርት ዘመን ጀምሮ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል። ሆኖም በቀጣዩ የትምህርት ዘመን ትምህርት የሚሰጠው በነባሩና በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት እንደሆነ ኃላፊው ጠቁመዋል።

በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ከተማ መስተዳድሩ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ተማሪዎችን ተቀብሎ በማስተማር መቆየቱንና የአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ በ44 ትምህርት ቤቶች ውስጥ የተጀመረው የሙከራ እንቅስቃሴ ውጤታማ እንደነበር ተናግረዋል።

አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በይዘት ላይ የነበረውን የመታጨቅ ችግር ከመቅረፉ ባለፈ ተግባር ተኮር እውቀት ከማስጨበጥ አኳያ ፋይዳው የጎላ መሆኑም ተነግሯል።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አንደኛ ደረጃ እስከ 6ኛ ክፍል፣ መካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍል፣2ኛ ደረጃ(9ኛ-12ኛ) ክፍል እንደሚሆን የገለጹት አቶ አድማሱ፤ በ6ኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና፣ በ8ኛ ክፍል አገር አቀፍ ፈተና እንዲሁም በ12ኛ ክፍል የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መግቢያ ፈተና እንደሚሰጥ አስገንዝበዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርትና ስልጠና ጥራት፣ ቁጥጥር ባለሥልጣን ምክትል ሥራአስኪያጅ ወ/ሮ ፍቅርተ አበራ በበኩላቸው፣ ነባሩ ሥርዓተ ትምህርት ሰፊ ክፍተቶች እንዳሉትና አተገባበሩም በተለይም በግል የትምህርት ተቋማት ወጥ ባለመሆኑ በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን ገልጸው፣ በአንጻሩ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት አገር በቀልና ዓለም አቀፋዊ እውቀት በውል ያቀፈ በመሆኑ ትምህርት አሰጣጡ ወጥ እንዲሆንም በተገቢው ይሠራል ብለዋል።

በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት በእውቀት የታነጸና ሙሉ ስብዕና ያለው ትውልድ ለማፍራት ተግባር ተኮር አሳታፊ ለማድረግ የመማር ማስተማር ሂደቱ በደንብ መቃኘቱን የተናገሩት ወ/ሮ ፍቅርተ፣ ለትምህርት ይዘትና አሰጣጥ ብቻ ሳይሆን ለምዘና ሥርዓትም ተገቢው ትኩረት በመሰጠቱ የግልም ሆነ የመንግሥት ትምህርት ተቋማት ለተግባራዊነቱ ራሳቸውን ማዘጋጀት እንደሚገባቸው አስገንዝበዋል።

ነገር ግን በቂ ልምድና እውቀት ያላቸው መምህራን እጥረት ባለበት እና ላሉትም ቢሆን ቢሮው በውል ስልጠና ባልሰጠበት ሁኔታ አዲሱን ሥርዓተ ትምህርት በሚፈለገው ልክ ተግባራዊ በማድረግ አስፈላጊውን ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ እንደሚሆን የመድረኩ ተሳታፊዎች ያላቸውን ሥጋት ገልጸዋል።

ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ሻምፒዮንስ አካዳሚ የመጡት አቶ ነብዩ ልዑል ከዚህ በፊት በተለይ በግል ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ሥርዓተ ትምህርቶች ተግባራዊ እንዲደረጉ ሥርዓተ ትምህርቱ ሰፊ ክፍተት እንደነበረ አንስተው፣ ያሁኑም ቢሆን በተለይ ለአንደኛ ክፍል የተዘጋጀው የእንግሊዝኛ መጽሐፍ የተማሪውን ዕድሜ ያላገናዘበ እንደሆነ መታዘብ መቻላቸውንና ተመሳሳይ ታሪክ እንዳይደገም ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ መክረዋል።

በጉለሌ ክፍለከተማ ከአጼ ተክለጊዮርጊስ ሚስዮን ትምህርት ቤት የመጡት አቶ አወቀ ለሜሳ በበኩላቸው ሥርዓተ ትምህርቱ ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ብቻ ሳይሆን የትምህርት ባለሙያዎች ጭምር በመሆናቸው ወደ ውስጥ ማየት ተገቢ መሆኑን አመልክተዋል።

# ኢትዮጵያ በኃያላኑ ፍጥጫ የኢኮኖሚ ቀውስ እንዳይገጥማት ዘላቂ መፍትሄ እንደሚያስፈልጋት ተጠቆመ

**አዲሱ ገረመው**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በየጊዜው በሚስተዋለው የኃያላን አገራት የጦርነት ፍጥጫ ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ቀውስ እንዳይገጥማት ዘላቂ መፍትሄ ያስፈልጋታል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ተመራማሪው ዶክተር ጀማል ሙሐመድ ገለጹ።

በኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት የዘርፉ ተመራማሪ የሆኑት ዶክተር ጀማል ሙሐመድ የቻይናና የአሜሪካን ፍጥጫ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ አስመልክተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር በነበራቸው ቆይታ፤ የኃያለን አገራት ፍጥጫ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሥርዓት ሰንሰለትን እያዛባ መሆኑን ገልጸዋል። ለአብነትም የዩክሬንና የሩሲያ ጦርነት የኃያላኑን አጋራት ሳይቀር ኢኮኖሚ ያዛባ መሆኑ ለዚህ ማሳያ እንደሆነ ጠቅሰዋል። ኢትዮጵያ በኃያላኑ ፍጥጫ የኢኮኖሚ ቀውስ እንዳይገጥማት ዘላቂ መፍትሄ ያስፈልጋታል ሲሉም መክረዋል።

በአሜሪካና በቻይና መካከል በሚፈጠር ፍጥጫና እሰጥ አገባ «እኔን ተከተል» የሚል ነገር ሲመጣ በታዳጊ አገራት ላይ ተጨባጭ የሆነ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ይገጥማል ያሉት ዶክተር ጀማል፤ የአሁኑ የኃያላኑ ፍጥጫ ከሩሲያና ከዩክሬን የበለጠ ቀውስ ሊያስከትል እንደሚችል ነው የጠቆሙት። ጦርነት ውስጥ የገቡ አገራት ለዓለም ገበያ የሚያቀርቡት ምርት ችግር ሲገጥመው በመላው ዓለም ሥርዓቱ እንደሚዛባና የአቅርቦት እጥረት እንደሚከሰት ገልጸዋል።

ዶክተር ጀማል፤ የሁለቱ አገራት ፍጥጫ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ሊያባብሰው እንደሚችል ጠቁመው፤ ቻይና ምርቷ ከቀነሰ እንዲሁም የፋብሪካ ዕቃዎች ከቻይና ወደ አፍሪካ የማይመጡ ከሆነ አጣብቂኝ ውስጥ ሊያስገባ እንደሚችል ጠቅሰዋል።



ዶክተር ጀማል ሙሐመድ

ቻይና ለአፍሪካና ሌሎች አህጉራት በቅናሽ ዋጋ ምርት የምታቀርብ፣ በመላው ዓለም በተለይም በታዳጊ አገራት የመሠረተ ልማት ሥራዎችን የምትሠራ እንደመሆኑ ተጽዕኖው ከፍተኛ ነው ብለዋል።

አሜሪካና ምዕራባውያን በቻይና ላይ ማዕቀብ ቢጥሉ፤ ሌሎች አገራት በተለይም አፍሪካውያን አሜሪካን አሊያም ቻይናን የመምረጥ ችግር ውስጥ ሊገቡ እንደሚችሉም ዶክተር ጀማል ተናግረዋል። አሜሪካ በተለያዩ ተራድኦ ድርጅቶችና በዓለም ባንክ በኩል እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የሰብዓዊ እርዳታ የሚፈልጉ አገራትን ልትጎዳ እንደምትችልም አመላክተዋል። ተቋማቱ የአሜሪካ ተጽእኖ ካለባቸው ለአፍሪካ አገራት የሚሰጡትን እርዳታና ብድር ሊያቋርጡ ይችላሉ ነው ያሉት።

በአንጻሩ ደግሞ ቻይና በአፍሪካ ኢንቨስት የምታደርገውና የምትሠጠው ብድር ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት ያደረጉባቸው በርካታ ኩባንያዎች እንዳሉና በኢትዮጵያ እያመረቱ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቧቸው ምርቶች ብዙ መሆናቸውን አንስተዋል። በመሠረተ ልማት ሴክተሩም ቢሆን ቻይና ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እንዳላት ጠቅሰዋል። ይህ በጦርነቱ ተጽዕኖ ሊቆም ይችላል የሚል ስጋት እንዳላቸውም ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ አጣብቂኝ ውስጥ ልትገባ ትችላለች ብለዋል።

ፍጥጫው እየተባባሰ የሚሄድ ከሆነ የትኛውን አማራጭ ፖሊሲ መጠቀም እንደሚገባ ለአገራት አስቸጋሪ መሆኑን በመግለጽ፤ ኢትዮጵያ ከሁለቱ አጋራት ጋር ባላት የጠበቀ ቁርኝት ምክንያት አንዱን ደግፋ ሌላውን ማጣት ስለማይገባት ገለልተኛ አቋም ማንጸባረቅ አለባት ሲሉ መክረዋል። በሁለቱ አገራት መካከል ያለው ችግር በሠላም እንዲፈታ ፍላጎት ከማሳየት ውጪ ያለውን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ወዳጅነት ለማስቀጠል የአንዱን ፍላጎት በሚነካ መልኩ ጣልቃ መግባት እንደሌላበትም ተናግረዋል።

እንደ ዶክተር ጀማል ገለጻ፤ ችግሩ መቼ እንደሚፈታ አይታወቅም። በመሆኑም ኢትዮጵያ መሰል ችግሮች ተጽዕኖ እንዳያደርሱባት ዘላቂነት ያለው መፍትሄ አስቀምጣ መሥራት ይኖርባታል። ከዚህ ውስጥም በዋነኝነት በምግብ ራስን መቻል ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርባታል። በምግብ ራሱን የቻለ ሕዝብ ማዕቀብ ቢጣልበት እንኳን የመቋቋም አቅም ይኖረዋል። ስለዚህም በግብርናው ዘርፍ ትልቅ ሥራ ይጠበቃል። ከዚህም በተጨማሪ ከሌሎች አፍሪካ አገራት ጋር የንግድ ትስስር የበለጠ ማጠናከር ይኖርባታል። ከኢትዮጵያ የተሻለ የፋብሪካ ምርት ካላቸው አገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ማጠናከርና የንግድ አማራጮችን መከተል ያስፈልጋል። የአገር ውስጥ ፋብሪካዎችም የበለጠ ገበያ ሊፈጠርላቸው ይገባል።

# ማህበሩ ኢትዮጵያውያን ከልዩነቶቻቸው ይልቅ ለአንድነታቸው አጽንኦት እንዲሰጡ አሳሰበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-የኢትዮጵያ የታሪክ ባለሙያዎች ማህበር ኢትዮጵያውያን ከልዩነታችን ይልቅ ለአንድነታችን፤ ካለፈው ይልቅ ለአሁኑ አጽንኦት መስጠት እንደሚገባቸው አሳሰበ።

የኢትዮጵያ የታሪክ ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ «ትስስርና መስተጋብር በኢትዮጵያ ታሪክ» በሚል መሪ ሀሳብ ትናንት በተዘጋጀ አውደጥናት ላይ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ረጅምና ደማቅ ታሪክ ያላት አገር ብትሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ታሪክ የፖለቲካ ግብግብ አውድማ እየሆነ መጥቷል።

ይህም በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶችና አለመግባባቶች እንዲፈጠር አድርጓል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም ከልዩነታችን ይልቅ ለአንድነታችን፤ ካለፈው ይልቅ ለአሁኑ አጽንኦት መስጠት ይጠበቅብናል።

በ1983ዓ.ም የተደረገው የሥርዓት ለውጥ መፈክሩ «ህብረ ብሔራዊ አንድነት» ወይም «አንድነት በብዝሀነት» ቢሆንም አንድነቱ ሳይሆን ብዝሀነቱ ገኖ ወጥቷል ብለዋል።

የታሪክ ሰነዶች እና ማስረጃዎች የሚያመለክቱት የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እና ክልሎች ምንም እንኳን የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ ባህርያት እና ተቋማት ቢኖራቸውም በብዙ መንገድ እርስ በእርስ የተሳሰሩና የተጋመዱ መሆናቸውን ፕሮፌሰሩ ጠቅሰዋል።

ህብረ ብሔራዊ ትስስር የተሞላው የታሪክ ሀቅ በተለይም ብሔራዊ መግባባት ለመፍጠር እንቅስቃሴ በተጀመረበት በአሁኑ ወቅት ጎልቶ ሊወጣ ይገባል ነው ያሉት።



ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ

ማህበሩ ከተቋቋመበት አላማዎች አንዱ ታሪክና የታሪክ ትምህርት ለብሔራዊ መግባባት ስለሚውልበት ሁኔታ ሙያዊ አስተዋጽኦ ማበርከት ሲሆን የዛሬው መድረክም ለብሔራዊ መግባባት የድርሻውን ለማበርከት ያለመ ነው ብለዋል።

ማህበሩ በቀጣይ መሰል መድረኮችን እንደሚያካሂድ ገልጸው መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ለማህበሩ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

በመድረኩ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ፣ የአገራዊ ምክክር ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርአያ፣ እንዲሁም በተለያዩ የትምህርት ተቋማት የሚሠሩ ምሁራን ተገኝተዋል።

## «የትምህርት ጥራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መንገድ ቁጥጥር እንዲያደርግ ወደ ባለስልጣን እንዲያድግ ተደርጓል።

ከዚህ በፊት በነበረው አደረጃጀት ባለስልጣኑ የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ስለማይቆጣጠር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ ቁጥጥር በሚያደርግበት ወቅት ተናቦ ስላልተሠራ አንዳንዶች ቴክኒክ ተቋም ነን እያሉ የማምለጫ መንገድ ይፈልጉ እንደነበር ጠቅሰዋል።

ዶክተር አንዷለም እንዳሉት፤ የውጭ አገራት ዩኒቨርሲቲዎች የሚወዳደሩበት አንደኛው መስፈርት የቀድሞ ምሩቃን ብለው ተማሪዎቻቸውን ሁልጊዜ ይከታተላሉ። ምን ያህሉ ኢንቨስት እንዳደረጉ፤ ምን ያህሉ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም እንደቀጠሉ፤ ምን ያህሉ ፒኤችዲ እየሠሩ እንደሆነ፤ ምን ያህሉ በግልና በመንግሥት ተቋማት እንደተቀጠሩ፣ ወዘተ በመከታተል በትምህርት ጥራት ላይ ውጤታማ ሆነዋል።

ከዚህም አልፎ የስንቶቹ ተቋማት ምሩቃን ዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ ገብተው እየሠሩ እንዳሉና ስኬታማ እንደሆኑ ጭምር የሚከታተሉበት መንገድ መኖሩን የጠቀሱት ዶክተር አንዷለም፤ የኢትዮጵያ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ከውጭ አገራት ተሞክሮ ሊወስዱ እንደሚገባም ገልጸዋል።

ከአገሪቱ ሕዝብ ከ30 በመቶ በላይ የሚሆነው በትምህርት ገበታ ላይ እንዳለ የገለጹት ዶክተር አንዷለም፤ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ባለስልጣኑ ከሚሠራው መደበኛ ሥራ ባሻገር ከተማሪው፣ እስከ ወላጁ፤ ከመደበኛ ትምህርት ቤት እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ድረስ ያለው አደረጃጀት፣ ምሁራን የሁሉንም ድርሻ የሚጠይቅ ሰፊ ሥራ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ከ27 አመት ጀምሮ በትምህርት ጥራት ላይ የተሠራው ሸፍጥ አገሪቱ ከፍላ የማትጨርሰውና አንድ ትውልድ የሰነጠቀ እንደሆነም ዶክተር አንዷለም ጠቁመዋል። አንድ ትውልድ ማንበብ፣ መጻፍ፣ የራሱን መብትና ግዴታ ማስጠበቅ የማይችል ትውልድ እንዲፈጠር አድርጓል። አሁንም በሚያስደነግጥ ሁኔታ አንዳንድ ተቋማት ላይ ተማሪዎች የሚከራከሩት ባገኙት የ «ኤ» ብዛት ነው። ተማሪው በውጤቱ ልክ አውቋል ወይ ሲባል ግን የገንዘብ ማግኛ ሲሆን እየታየ ነው ብለዋል።

ዶክተር አንዷለም እንደገለጹት፤ አንድ ተማሪ ከትምህርት ቤት ተመርቆ ከወጣ በኋላ በሙያው ሲሰማራ ችግር ሲፈጠር እየተስተዋለ ነው። ለምሳሌ «አካውንታት ሆኖ ያላተረፍከውን አትርፈሃል ብሎ ግብር ያስከፍላል»፣ በኢንጅነሪንግ ተመርቆም የግንባታ ጥራት ችግር ይታያል፤ ለምሳሌ በጎርፍ ስትቸገር ይታያል፣ ይህ ክረምቱ የተለየ ሆኖ ሳይሆን የተሠሩ የውሃ ማስተላለፊያ ቱቦዎች፣ ልማቶች ፍሳሹን በትክክል ማስተናገድ እንዳይችሉ ሆነው ስለተገነቡ ነው። እንደ አገር የሚታዩ ችግሮች በሙሉ የትምህርት ውጤቶች ናቸው። ስለዚህ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ ሁሉም ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል።



## የአስተዳደር ወሰኑን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሃይማኖት አባቶች፣ አባገዳዎች፤ አገር ሽማግሌዎች እና የተለያዩ የኅብረተሰብ ተወካዮች ተሳትፈዋል። የመድረኩ ዋነኛ ዓላማ የተደረሰው ስምምነት የሕዝቦችን አንድነትና አብሮ ማደግ በሚያጠናክር መልኩ እንዲተገበር ማድረግ ነው።

በአዲስ አበባ ከተማና ፊንፊኔ ዙሪያ ኦሮሚያ ልዩ ዞን መካከል የአስተዳደር ወሰን ባለመኖሩ ምክንያት በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ሲነሳ መቆየቱም ነው በመድረኩ የተገለጸው። በተለይ መሠረተ ልማት ዝርጋታና ወሳኝ የሆኑ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት እንዲሁም የመሬት ወረራን ጨምሮ ሕገ ወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠር አስቸጋሪ ሁኔታ ፈጥሮ መቆየቱን ነው የመድረኩ ተሳታፊዎች ያነሱት። ከተማ አስተዳደሩና ልዩ ዞኑ ተቀናጅተውና ተደጋግፈው በጋራ እንዳያድጉና እንዳይለሙ እንቅፋት ፈጥሮ መቆየቱም እንዲሁ።

በመሆኑም የአስተዳደር ወሰን ጉዳይን በዘላቂነት ለመፍታት እንዲቻል ከከተማ አስተዳደሩና ከልዩ ዞኑ የተውጣጣ የጋራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጥልቅ ጥናት ማካሄዱም ተገልጿል።

የአስተዳደር ወሰን መካለልም የሕዝቦችን ማህበራዊ ትስስር የሚያጠናክር፣ ዘላቂ የሕዝቦችን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ መሆኑም ነው የተገለጸው።

ይህ የወሰን ማካለል ሂደት ተግባራዊ ሲደረግም የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥት፣ የኦሮሚያ ክልል ሕገ-መንግሥትና የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር እንደመነሻ መወሰዱ ተገልጿል። የአስተዳደር ወሰኑ በሕዝቦች ስምምነት መሠረት መካለል ለዘላቂ ሰላምና ልማት ከፍተኛ ሚና እንዳለውም ተጠቅሷል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ የአስተዳደር ወሰን ለዘመናት ምላሽ ሳይሰጠው መቆየቱን አስታውሰዋል። በመሆኑም የአስተዳደርና ወሰን ጥያቄ የሕዝቦችን አብሮ የመኖር እሴት ለማጎልበት በማሰብ ተግባራዊ መደረጉን ጠቁመዋል።

ይህ ውሳኔም ከወሰን ባሻገር የሕዝቦችን አብሮ መኖር እሴት የሚያጠናክር፣ አብሮነትን የሚያጎለበትና ሁለቱንም ነዋሪዎች ተጠቃሚ የሚያደርግ ነውም ብለዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው ይህ ውሳኔ ተግባራዊ በሚደረግበት ጊዜ በሁለቱም አካባቢ እየተሰጠ ያለው አገልግሎት እንደቀደመው ሁሉ የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል።

በሌላ መልኩም የአካባቢዎቹን ሰላምና ደህንነት የማረጋገጥ ተግባር በቁርጠኝነት የሚሠራ መሆኑን ጠቁመው፣ በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችም ባሉበት የሚቀጥሉ መሆኑን ተናግረዋል።

የመድረኩ ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየትም ውሳኔው የሕዝቦች አብሮ የመኖር እሴት የሚያጠናክር መሆኑን ተናግረዋል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርና በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን የቴክኒክ ኮሚቴ በማቋቋም ጉዳዩን በጥንቃቄ እንዲያዩትና ስምምነት ላይ እንዲደርስ ማድረጋቸው ተቀባይነት ያለው ጉዳይ መሆኑና የቴክኒክ ኮሚቴው ጉዳዩን በኃላፊነት ወስዶ የሕዝቦች ጥያቄ ምላሽ እንዲያገኝ በማድረጉ ሊደነቅ ይገባልም ብለዋል።

## ኢንተርፕራይዞችና ሥራ ፈጣሪዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፈጣሪዎችን ቁርጠኛ ውሳኔ ጭምር እንጂ የመንግሥትን ጥረት ብቻ የሚጠይቅ አይደለም ሲሉም አክለዋል።

የሥራና ክሂሎት ሚኒስቴር ሚኒስትር ሙፈሪያት ካሚል በበኩላቸው፤ በራሳቸው ጥረት የመንግሥትን እገዛ ተጠቅመው፣ የሌሎች ባለድርሻ አካላትን እገዛ ስንቅና ግብዓት አድርገው ለዕውቅና ፕሮግራም የበቁ ተሳታፊዎች የአገሪቱን ኢኮኖሚ መሠረት ለመጣል ተስፋ የሚጣልባቸው መሆናቸውን ገልፀዋል።

በተለይ በላቀ አፈፃፀም የተሸለሙትን፤ በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት መካከል ልቀው የተገኙትን ተሸላሚዎች ተምሳሌት እንዲሆኑ ለማስቻል ታልሞ የተዘጋጀ መድረክ መሆኑን በመጥቀስ ሽልማቱ በአነቃቂነቱ ትልቅ እሴት አካይ የሆነ ውጤት ይኖረዋል ብለን እንጠብቃለን ብለዋል።

ያለፉት አሥር ወራት በአንድ በኩል መንግሥት ለዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ያሳየበት ነው ያሉት ወይዘሮ ሙፈሪያት፤ በሌላ መንገድ ደግሞ ለሥራ ፈጠራዎችና ለሥራ ዕድል ተግዳሮት ለመለየትና ተግዳሮቶችን ነቅሶ አውጥቶ ለመፍታት ጥረት ሲደረግ መቆየቱን ጠቁመዋል። 2014 በጀት ዓመት ምቹ መደላድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ሰፋፊ የለውጥ ሥራዎችን ለመሥራት ከባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ርብርብ ያደረግንበትና መሠረት መጣል የጀመርንበት ዓመት ነውም ሲሉ አክለዋል።

በ2012 ዓ.ም የመጀመሪያው ብሔራዊ የሥራ ጉባዔ ተካሂዶ በ2013 ዓ.ም በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ሳይካሄድ ቀርቷል። በመሆኑም ሁለተኛው ዙር የሥራ ጉባዔ በ2014 ዓ.ም «ዘላቂ ሥራ ለብሩህ ነገ» በሚል መሪ ሃሳብ ነሐሴ 9 እና 10/2014 ዓ.ም ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ መዝጊያ ላይ በዘርፉ ጥሩ አፈጻጸም ላስመዘገቡ ኢንተርፕራይዞች እና አስፈፃሚ ተቋማት፣ የማዕከል አገልግሎት ሰጪዎች እና የሥራ ፈጠራ ውድድር አሸናፊዎች ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እጅ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በዕለቱ ለ61 የማዕከል አገልግሎት ጣቢያዎች፣ ለ138 ወደ መካከለኛ ደረጃ ለተሻገሩ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ለ12 የቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና የሥራ ፈጠራ ውድድር አሸናፊዎች ሽልማት ተበርክቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የፈተና ማግስት ሳቅ!

በፈተና ውስጥ ያላለፈ ወይም የማያልፍ ማኅበረሰብ፣ ሀገርና ሕዝብ አልነበረም የለምም። እንደየዘመኑ ዘመን አሻጋሪ ፈተናዎችን መጋፈጥ የማይቀር ነው። ፈተናዎችን አሸንፎ መውጣት ወይም በፈተናዎች ተሸንፎ መውደቅ የአንድ ማኅበረሰብ ሀገርና ሕዝብ ቀጣይ እጣ ፋንታ አመላካች ነው ።

በተለይም አንድ ሀገርና ሕዝብ ከአንድ የታሪክ ምዕራፍ ወደ ቀጣይ የታሪክ ምዕራፍ የሚያደርገው ጉዞ በብዙ ፈተናዎች የተሞሉ ናቸው። ፈተናዎቹ በዋነኛነት በአሮጌ እና በአዲስ አስተሳሰብ መካከል የሚደረጉ ፤ ሊያስከፍሉ የሚችሉትም ዋጋ እልህ አስጨራሽ ከመሆን ባለፈ የመስዋዕትነትን ጥግንም የሚጠይቁ ናቸው ።

የታሪክ መዛግብት እንደሚተርኩት ከሆነ ደግሞ እነዚህ ፈተናዎች ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የሚደርሱት በማኅበረሰብ ውስጥ መሰረታዊ ሽግግር ማምጣት የሚያስችሉ/ማኅበረሰብን ከአንድ የታሪክ ምዕራፍ ወደቀጣይ የታሪክ ምዕራፍ የሚያሻግሩ / አስተሳሰብን መሰረት ያደረጉ የለውጥ ንቅናቄዎች በሚከሰቱባቸው አጋጣሚዎች ነው።

ወቅቱ አሮጌው አስተሳሰብ በማህበረሰቡ ውስጥ ከቆየበት ረጅም ዘመን አንጻር ለራሱ የፈጠረው መደላደልና በመደላደሉ መተማመን የፈጠረው የማኅበረሰብ ክፍል እና ቡድኖች ከአስተሳሰቡ የሚገኘውን ትሩፋት ለማስቀጠል የሚያደርጉት የሞትና የሽረት ትግል ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የሚደርስበት ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የአሮጌው አስተሳሰብ መሻገት የፈጠረው ማኅበራዊ ቀውስ እና ቀውሱ የፈጠረው የለውጥ መንፈስ ሕይወት ዘርቶ ማህበራዊ መሰረት እንዲኖረው የሚደረገው ትግል እልህ አስጨራሽ በሆኑ ማኅበራዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች እየተፈተነ የሚጠራበት ነው ።

ይህ ታሪካዊ ክስተት በኛም ሀገር ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ የሚታይ ተጨባጭ እውነታ ሆኗል። ሃገሪቱ በአንድ በኩል ሃገርና ህዝብን ለዘመናት ብዙ ዋጋ ያስከፈለውንና እያስከፈለ ያለውን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ ለማስቀጠል በሚጥሩ ቡድኖች፤ በሌላ በኩል ይህን አስተሳሰብ በማስወገድ አዲስ አሻጋሪ አስተሳሰብ ለማስረጽ በሚሹ ሀይሎች መካከል ግልጽ በሆነ መራራ ትግል ውስጥ ነች።

በተለይም የለውጥ ኃይሉ ይዞት የተነሳው ሀገርን በከፍታ ውስጥ የማሰብ ሃገራዊ ራዕይ የውጪ ኃይሎችም ጭምር ሀገራዊ የፈተና ምንጭ እንዲሆኑ የጋበዛቸው ሲሆን፤ በዚህም ሀገርና ህዝብ ለመክፈል የተገደዱት ዋጋ ለግምት የማይመች እልህ አስጨራሽ እንዲሆን አድርጎታል ።

ባለፉት አራት የለውጥ ዓመታት እንደ ሀገር ያገጠሙን ፈተናዎች የሀገርን ህልውና ስጋት ውስጥ የከተቱ ፤የሕዝቦችን ለዘመናት የቆየ ተቻችሎ አብሮ የመኖር እሴት በብዙ የጥፋት ትርክቶች በመመረዝ በህዝባችን አንድነት ውስጥ የነበረውን ኃይል ለመናድ ከፍ ያሉ ሴራዎች የተገመዱባቸው ናቸው።

ዓለም ባልተገባ ራስ ወዳድነት ከህዝባችን ፊቱን ያዞረበት ፤በርግጥም ፍትህና ፍትሃዊነት በተለይም በምዕራቡ ዓለም የፖለቲካ ዲስኩር ማድመቂያ ያለፈ ትርጉም እንደሌለው መላው ህዝባችን በተጨባጭ በራሱ ጉዳይ ያረጋገጠበትን ታሪካዊ አጋጣሚ ያስተናገደባቸው ናቸው።

ታሪካዊ ጠላቶቻችን የሃገር ውስጥ ባንዳዎችን በመጠቀም ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ሃገርን የፈተና መድረክ ያደረጉበት ፤በዚህም ዜጎች ለሞት ለመፈናቀልና ለስደት የተዳረጉባቸውን ክፉ ቀናትን በመፍጠር ሕዝባችን በልቡ ውስጥ የሰነቃቸውን በተስፋ የተሞሉ ነገዎች ለመግደል በተቻላቸው ሁሉ ፈተና ሆነው የተከሰቱበት ነው።

እንደ ሃገር አበቃላቸው ፤እንደ ሕዝብ እርስ በርስ ሊተላለቁ ነው የሚሉ የሟርት ትርክቶች በዓለም አቀፍ መድረኮች ሳይቀሩ አጀንዳ የሆኑባቸው ፤ይህንኑ ትርክት ስጋና ደም አልብሶ የሚጨበጥ ታሪክ ለማድረግ ብዙ የተሰራባቸው ዓመታት ናቸው ።

በተለይም የለውጥ ኃይሉ ይዞት የተነሳውን ከፍያለ ሀገራዊ ራዕይ ትርጉም አልባ እንዲሆን ከተራ የመንደርተኝነት ትርክት እስከ አደባባይ ሟርት በዘለቀ የክፋትና የጥፋት ጥግ ፋታ የለሽ ፈተና ውስጥ እንዲገባ የተደረገበት ነው።

ፈተናዎቹ እንደታሰበው ሳይሆን የለውጥ ኃይሉንም ሆነ መላውን ህዝባችን ጠንክሮ እንዲወጣ ፤ከእያንዳንዱ ፈተና በስተጀርባ ያለውን የተስፋውን ስኬት እያሰላ በጽናት እንዲቆም የተሻለ እድል በመፍጠር ለዛሬዋ አዲስ የተስፋ ቀን አሻግረውታል።

መላው ህዝባችን የተንሰላሰሉ ፈተናዎችን ከፍ ባለ ጽናት በስኬት እየተወጣ በየዕለቱ የተስፋይቱ ጸሐይ ተጨማሪ ብርሀን እየተላበሰች ከፈተና ኮረብታዎች ውስጥ ወጥታ የሀገሪቱን የሰማይ አድማስ የምትሞላበትን የታሪክ ምዕራፍ እየጻፈ ነው።

ሕዝባችን በብዙ ተስፋ አምጦ የወለደው ለውጥና ለውጡ በየቀኑ በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ እየሄደበት ያለው የስኬት /የድል መንገድ ከፈተናዎች ማግስት ያለውን ሳቅ የሚስቅበትን እድል ፈጥሮለታል ።

ይህ በይቻላል መንፈስ ተነስቶ እየሄደበት ያለው የለውጥ መንገድ እና እያስመዘገበው ያለው ስኬት የቱንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍለው፤ ከከፈለው ዋጋ በስተጀርባ ዛሬ ላይ የጀመረው ሳቅ ከፈተና ማግስት የሚገኝ በብዙ የመከራ ምጥ የሚወለድ ትውልድን የሚያሻግርና ከትውልዶች ጋር አብሮ የሚሻገር ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የምስጋና ባህል ለሀገር ያለው ጠቀሜታ......

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

በህይወታቸው ርከት ያሉ ሰዎች ራሳቸውን በምስጋና ውስጥ የደበቁ እንደሆኑ ታውቃላችሁ? በህይወት ሁሉን አጥተው ከስረው የሚኖሩ ራሳቸውን ከምስጋና ያራቁ እንደሆኑስ? ምስጋና የነፍሶች ህብስት ነው። የትም መቼም በእያንዳንዳችን ህይወት ውስጥ ሊኖር የሚገባው ትልቅ እውነት ነው ። በዚህ ራስ ወዳድ በሆነ አለም ላይ ራሳችንንም ሌሎችንም እንባርክበት ዘንድ የተሰጠን ጸጋችንም ነው። አብዛኞቻችን መኖር ምን እንደሆነ አናውቀውም ዝም ብለን ነው የምንኖረው ለዚህም ከስረንና እርባና ቢስ ሆነን እንኖራለን። ከምስጋና የራቀ ህይወት ማር እንደሌለው ቀፎ ባዶ ነው።

የመኖር ዋጋው ጥልቅ ነው..ብዙዎች በጥላቻና በመገፋፋት በሚኖሩበት በዚህ ሰዓት የምስጋናን ጥቅም ተረድተው በልዕልና የሚኖሩ እንዳሉም አውቃለሁ። እነሱ ምን ያክል እድለኛ እንደሆኑ ሳስብ እቀናባቸዋለሁ። ምስጋና ህይወትን ውብ የምናደርግበት አምላካዊ ጥበባችን ነው። አድናቆት የሌሎችን አለም፣ የሌሎችን ህይወት የምናደምቅበት፣ በርቱ ከዚህም በላይ ስሩ ብለን እውቅና የምንሰጥበት ሰውኛ ግብራችን ነው። የሰዎችን ልብ በነጻ የምንባርክበት፣ በነጻ የምንቀድስበት መላችን ነው ::

ከሁሉ በፊት የሌሎችን ህይወት የምንባርክበት መልካም አስተሳሰብ ያስፈልገናል። ሁሉም መንገዶች ለቅን ልቦች ክፍት ናቸው። እስካሁን ድረስ የተዘጉ መንገዶቻችን ካለፍቅር በጥላቻ የተጓዝንባቸው ስለሆኑ ነው። በእርግማንና በወቀሳ ስለተራመድንባቸው ነው። እንደ ሀገር በመኖር ውስጥ ትልቅ ዋጋን ሊያስገኙልን የሚችሉ በረከቶች የቱ ጋ እንዳሉ ገና አላወቅንም። መልካም ህይወት በቁስና በገንዘብ የሚገኝ የሚመስለን ብዙዎች ነን። በህይወት ውስጥ በገንዘብ የማይመለሱ ነፍሳዊ ጥያቄዎች እንዳሉ አናውቅም::

የሁሉም ጥያቄዎች መልስ አንድ ቦታ ነው ያለው እርሱም ቅን ልብ ውስጥ ነው። ቅን ልብ ደግሞ በምስጋና በፍቅር በይቅርታ የተሞላ ነው። ቅንነትና መልካምነት አብሮን እስከሌለ ድረስ እንቅፋቶቻችን ሁሉ የሚጥሉን ነው የሚሆኑት። የነካነው የሚገማ፣ የረገጥነው የሚከረፋ ነው የሚሆነው። ቅን ልቦች መራቂዎች ናቸው፣ ቅን ልቦች በራሳቸው ላይ እንዲሆን የማይፈልጉትን በሌሎች ላይ አያደርጉም። ቅን ልቦች ለሌሎች የሚሆን ብዙ ፍቅር ብዙ እውነት አላቸው..ቅን ልቦች በሀሳባቸው በግብራቸው ፈርሀ እግዚአብሄር አለ።

በህይወታችን እንዲሁም በኑሯችን ምርጥ መሆን ከፈለግን ራሳችንን እያመሰገንንና እየተመሰገንን ልናገኘው ይገባል። በህይወታችን ድንቅና ስኬታማዎች መባል ከፈለግን ሞት የሌለበትን ህይወት ፍቅርን ልንለብስ ይገባናል። ያኔ ከራሳችን አልፈን በዙሪያችን ለቆሙ ሁሉ አስፈላጊዎች እንሆናለን። ያኔ የሌሎች ቁስል ያመናል፣ የሌሎች መከራ ይሰማናል። ምክንያቱም ፍቅርን እናውቃለንና። ያኔ ሌሎች ለእኛ እኛም ለሌሎች ምን ያክል አስፈላጊዎች እንደሆንን እንደርስበታለን። ያኔ የእውነት ሰው እንሆናለን። ጥላቻን ገድለን፣ ዘረኝነትን አውድመን በፍቅርና በምስጋና ሀይል አንድነትን በውስጣችን እናጸናለን::

የዚህ አለም ታላቁ ጥያቄ እኔ ማነኝ? ለምንድነው ሰው የሆንኩት የሚለው ነው። ይሄን ጥያቄ ሳንመልስ፣ በዚህ ጥያቄ ላይ ሳንረማመድ ዘመናዊነት አይጎበኘንም። ተመኝተን የሚሳካልን አንዳች አይኖርም። ይሄን ጥያቄ ሳንመልስ የሚኖረን እውቀትና ማስተዋል አይጠቅመንም። ታላቁ ፈላስፋ ሶቅራጠስ "ያልተመረመረ ህይወት ዋጋ የለውም ይላል"። እውነት ነው ያልተመረመረ...ያልተጠየቀ ህይወት ትርጉም የለውም። መኖራችን ዋጋ የሚያገኘው ለምን ሰው እንደሆንን ስናውቅ ብቻ ነው::

ራሳችንን በፍቅር ጠበል እንጥመቅ። በምስጋና ባህር እናርስ፣ በይቅርታና በውዳሴ ኩሬ ውስጥ እንንከር። እንረስርስ..ምስጋና በዝቶልን፣ ውዳሴ ተትረፍርፎልን እትት እንበል። ያኔ መኖር እንጀምራለን። በልዕልና እንኖር ዘንድ ለምን እንደተፈጠርን፣ በመኖር ውስጥም ስላሉ ለህይወት እጅግ አስፈላጊ ስለሆኑ ቁም ነገሮች ማወቅ አለብን። ዝም ብለን እንድንኖር አልተፈጠርንም። መልካም የሆነውን እንድንፈልግና እንድንከተል ነው ሰው የሆንነው። መልካም የሆነው ደግሞ ምስጋና ነው። ከሌሎች ጋር በፍቅር በመቻቻል መኖር ነው::

ምስጋና የስልጡን ማህበረሰብ መገለጫ ነው። ማመስገን ከሌሎች ልዩ መሆን ነው። ለሌሎች የሚሆን በረከት እስከሌለን ድረስ ራሳችንን ልዩና ምርጥ ሆነን አናገኘውም። በአስተሳሰባቸው የላቁ ሰዎች በልባቸው ውስጥ ብዙ ምስጋና አለ። በህይወታቸው ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች የስኬት ምንጫቸው ምስጋና ነው ። እነዚህ ግለሰቦች ደስተኛና ጤነኛም ናቸው። ወንዝ ዳር እንደበቀለ አበባ ለምለምና ብሩህ ናቸው። በተቃራኒው ምስጋናን የማያውቁ ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ ብዙ ባዶነት ያለባቸው ናቸው። በርሀ ላይ እንደበቀለ አበባ ጥመኛ። እስካሁን ድረስ የደረሱብን የህይወት ውጣ ውረዶች ሁሉ ካለበጎነት የሆኑ ናቸው። ሁሌም ጉድለታችን የፍቅር አለመኖር ነው...የደግነት የርህራሄ ማጣት ነው። ሌሎችን እስካላመሰገንንና በመልካም ስራችን እስካልተመሰገንን ድረስ መኖራችን ትርገም አይኖረውም::

እርግማንን ወቀሳን እንጸየፍ። አሁን ላይ የብዙዎቻችን ችግር ይሄ ነው። ከሚጠቅመን ይልቅ ለማይጠቅመን የበረታን ነን። አዲስ ልብና አዲስ መንፈስን እስካልተላበስን ድረስ ላመል ደስታ አይኖረንም። ደስታ የተግባር ውጤት ነው። ደስታ ከውስጥ የሚመነጭ የራስ የአስተሳሰብ ውጤት ነው። ደስታን ፍለጋ ሩቅ የሚሄዱ ሁሉ ውስጣቸው ፍቅር የሌለ፣ ምስጋናን ይቅርታን የማያውቁ ናቸው። የሰላም ሁሉ ስፍራው ልብ ነው። ሰው ልቡን ካነጻ መሳቂያ አያጣም። ማረፊያ ስፍራ አይቸግረውም። ችግር የሆነብን ልባችንን አለማጽዳታችንና ለፍቅርና ለምስጋና ቦታ ማጣታችን ነው።

የሚጠላ ልብ እግዚአብሄርን አያውቅም። መሞት የምንጀምረው መጥላት ስንጀምር ነው። በህይወታችን የመጣና እንዲመጣ የምንፈልገው ልክነት ሁሉ በአፈቀርን ሰሞን፣ አመሰግናለሁ ባልን ሰሞን፣ አሜንና ተመስጌን ባልን ቅጽበት የሆነና የሚሆን ነው። የእስካሁኑ ህይወታችን በጥላቻና በእርግማን፣ በትችትና በወቀሳ ያለፈ ነው። ከእንግዲህ አትርፈን እንጂ ከስረን መኖር አይኖርብንም። በእያንዳንዱ ማለዳ የምናገኛቸውን ሰዎች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደምናገኛቸው ሆነን ልንወዳቸውና ፍቅር ልንሰጣቸው ይገባል። ባለንና በሌለን ነገር ላይ ማመስገንን እንልመድ። በህይወታችን ለሆነውና እየሆነ ላለው ሁሉ አሜን እንበል።

የተለያዩ ሰዎች ስለምስጋና ብዙ ብለዋል። አሜሪካዊቷ ጥቁር ቢሊየነር ኦፕራ ዊንፍሬይ ስለ ምስጋና ስትናገር እንደህ ነበር ያለችው ‹ካለ ምስጋና ያለፈ ህይወት የለኝም። ሁልጊዜም ባለኝና በሌለኝ ነገር አመሰግናለሁ እላለሁ። የአሁኑ የስኬቴ ምስጢርም ማመስገኔ ነው እላለሁ። ምስጋና ያለኝን የማቆይበት የሌለኝን ደግሞ የምስብበት ሀይሌ ሆኖ ሁሌም አብሮኝ አለ›። ብላለች::

እኛ በብዙ ጭቆና በብዙ አፋኝ ስርዐት ውስጥ የኖርን ህዝቦች ነበርን። እውነት ናፍቃን አጎንብሰን ነበርን። አንድ የሀገር መሪ ከበታቹ ያሉትን ዝቅ ብሎ ሲያመሰግን እንደማየት ታላቅነት አለ ብዬ አላስብም። መሪዎች ሲያመሰግኑ አይተንም ሰምተንም አናውቅም። መሪ ሲቆጣና ሲቀጣ እንጂ ሲምርና ይቅርታ ሲያደርግ አናውቅም። ብርቃችን ነበር። ምክንያቱም ንጉስ ሲቆጣ ነዋ የምናውቀው።

ለውጥ ከማመስገን ይቅር ከማለት የሚጀምር ነው። በየትኛውም የእውቀት መስክ መርምሩት ምስጋና የምርጥ ሰዎች፣ የምርጥ መሪዎች መገለጫ ነው። ምርጥ ሰዎች ይቅር ይላሉ፣ ይቅር እንዲሉም ነው የተፈጠሩት። ምርጥ ያልሆኑ ደግሞ እንዲበቀሉ ወደዚህ አለም መጥተዋል። በምስጋናችን ማጣታችንን እናባረው ። በይቅርታ አርነት እንውጣ::

ጥላቻ የሞት መንደር፣ የክፋት ዋሻ ነው ምንም አይጠቅመንም። ከለመድነው እውነት መውጣት ይኖርብናል። እስካሁን በወቀሳ በትችት በእርግማን ኖረናል። በውሸት በአሉባልታ በማስመሰል ኖረናል። በመጥላት፣ በማንቋሸሽ፣ በመሳደብ በመናቅ ኖረናል ከመክሰር ባለፈ ያተረፍነው አንዳች ነገር ግን የለም::

ለማይጠቅመን ነገር ለምን እንለፋለን? ወደሚጠቅመን ለምን አንሄድም? ነጋችንን ብሩህ ይሆን ዘንድ ፍቅር ያስፈልገናል። ፍቅር ሞት የሌለበት አለም ነው። ሀገር አመስጋኝ ትውልድ ትሻለች። ፍቅር ህልማችን የሚሰምርበት፣ ተስፋችን የተሰወረበት ቅዱስ ስፍራ ነው። ምስጋና ክብራችን የተቀመጠበት ቦታ ነው። ስለዚህም ከፍቅርና ከምስጋና በቀር ራሳችንንና ህልማችንን የትም ልንፈልገው አይገባም። በቻልነው ባልቻልነውም አቅማችን አመስጋኝ እንሁን::

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ተጠየቅ

# ‹‹አመራሮችን ተመክተው መስሪያ ቤቱ የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ሳስመቀበል የሚያንገራግሩ ተቋማት አሉ››

**አቶ ታረቀኝ ገረሱ**

**የትምህርት እና ስልጠና ባለስልጣን የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር**

ምህረት ሞገስ

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራት ኤጀንሲ ስሙን ቀይሮ የትምህርት እና ስልጠና ባለስልጣን ሆኗል።ለምን ስሙን ቀየረ? ስሙን በመቀየር ብቻ የቁጥጥር ስራውን በተገቢው መልኩ መፈፀም ያስችላል ወይ? የጥራት ችግር ያለው በመላው አገሪቱ ሆኖ የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ላይ ብቻ ለምን ትኩረት ይደረጋል? የመንግስት ተቋማትንስ ለምን አልታዩም? እንዲሁም በባለስልጣን ስራ ላይ የባለስልጣናት ጣልቃ ገብነት እስከምን ድረስ ነው? በሚሉና በሌሎችም ተያያዥ ጉዳዮች ላይ የባለስልጣኑን የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ታረቀኝ ገረሱ ጋር ቆይታ አድርገናል ።መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራት ኤጀንሲ ስሙን ቀይሮ የትምህርት እና ስልጠና ባለስልጣን ተባለ ።ስም መቀያየር ለትምህርት ጥራት ቁጥጥርም ሆነ ክትትል ምን ፋይዳ አለው? ይልቅ ቁጥጥር እና ክትትሉ ላይ ማተኮር አይሻልም?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** መጀመሪያ ስለተቋሙ ሥራ እናንሳና ከዛ ወደ ስም ስያሜው መቀየር እንነጋገራለን። ተቋሙ መጀመሪያ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነት እና ጥራት ኤጀንሲ በሚል የተቋቋመው በ1995 ዓ.ም ነው። ከዛ ጀምሮ በአገሪቱ ውስጥ ያሉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጡትን ትምህርት እና ስልጠናዎችን አግባብነት እና ጥራታቸውን የማረጋገጥ ሥራ ዓላማን ይዞ ሲሠራ ነበር።ይሁንና ሌሎችም የተለያዩ ዋና ዋና ሥራዎችን ሲያከናውን ነበር።

የከፍተኛ ትምህርት የጥራት ኦዲት ሥራን ሲያከናውን ቆይቷል።የዕውቅና ፈቃድ አሠጣጥ ላይም ሲሠራ ነበር።የትምህርት ማስረጃዎችን ህጋዊነትን የማረጋገጥ እና የአቻ ግመታ ሥራም ሲሠራ ቆይቷል፡፡

እነዚህን ሥራዎች ሲሠሩ በጥራት ኦዲት ዙሪያም የተሠሩ ሥራዎች አሉ። በዛን ጊዜ እስከ 2011 ወደ 90 የሚደርሱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ጥራት ኦዲት አካሒደናል።የጥናት ኦዲት ሲደረግ አስር መስፈተርቶች አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ይቅርታ ሳቋርጦት።የትምህርት ጥራት ችግር እንደሚታወቀው በሁሉም ዘንድ አለ።እዚህ ላይ እናንተ የግሎቹን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ላይ እንጂ የመንግስትን ተቋማትን ጥራት አትከታተሉም እየተባላችሁ ትታማላችሁ።ይህንንም አያይዘው ይመልሱልኝ።ለምን የመንግስት የትምህርት ተቋማት ላይ ቁጥጥር አታደርጉም?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** አይ ጥራት ላይ የምንሰራው እና የምናየው ሁለቱም ላይ ነው። የግልም ሆነ የመንግስት ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችን እናያለን። ነገር ግን የመንግስቶቹ የትምህርት ተቋማት ልክ እንደኛ ኤጀንሲ ሁሉ የሚቋቋሙት በአዋጅ ነው። ኤጀንሲው በአዋጅ የተቋቋሙ ተቋማትን ለመቆጣጠር የተሰጠው ስልጣን ላይ ክፍተት ነበር። ነገር ግን በሁለቱም ላይ ይሠራል። እውቅና እና ፍቃድ ግን የሚመለከተው የግሎቹን ብቻ ነው።

በእርግጥ የመንግስቶቹን ለመቆጣጠር የአዋጅ ክፍተት ብቻ ሳይሆን ተቋሙ ራሱ ከውስጥ ችግር ነበረበት።ማለትም አደረጃጀት ፈጥሮ መቆጣጠር ላይ ድክመት እንደነበረበት አይካድም።

**አዲስ ዘመን፡- ድክመት ነበረበት ሲሉ እስኪ በደንብ ያብራሩት ? ተቋሙ ድክመት የነበረበት በምን በኩል ነበር?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** የአደረጃጀት ችግር ነበር። አደረጃጀቱ አሁንም ድረስ አላለቀም።ሌላው የባለሞያ ቁጥር ነው። ከተቋሙ ሥራ እና ተልዕኮ አንፃር የባለሞያው ቁጥር እጅግ በጣም ትንሽ ነው።ከ15 የማይበልጡ ባለሞያዎች ብቻ የሚኖሩበት ጊዜም ነበር።ባለሞያ ቢቀጠርም ወዲያው ይለቅ ነበር። ምክንያቱም እውነቱን ለመናገር የመስሪያ ቤቱ ሁኔታ በአጠቃላይ ጥሩ አልነበረም።

**አዲስ ዘመን፡- መስሪያ ቤቱ ጥሩ አልነበረም ሲሉ? ምን ማለት ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** አዎ! በግልፅ ለመናገር የመልካም አስተዳደር ችግር ነበር። ለዚህም ብዙ ማስረጃዎች አሉ።በተጨማሪ የአመራር ቁርኝነት ችግር ነበር።ይህንን ስል በፊት ምንም የተሠራ ነገር የለም ማለቴ አይደለም።ብዙ ተቋማት የጥራት ኦዲት ተደርገዋል። እስከ 2011 ዓ.ም 90 አካባቢ የሚሆኑ ተቋማት ፍቃድ እና እውቅና ተሰጥቷቸው እየተሠራ ነበር።የአቻ ግመታ ሥራም ሲሠራ ነበር።

የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ሥራም ሲሰራ ነበር።የመጀመሪያ የሆኑ መሠረታዊ ሥርዓት የመዘርጋት ሥራ ተሠርቷል።ነገር ግን የተቋቋመበትን ዓላማ ግብ ለመምታት ግን ችግሮች እንደነበሩ አይካዱም።ይህንን ህዝቡ ያውቀዋል።

የግል ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጥሩ የሚሠሩ እንዳሉ ሁሉ ምን ያህል ሰርተፍኬት የሚሸጡ እንዳሉ ይታወቃል።ከዛ አንፃር እውቅና እና ፈቃድ መስጠት ብቻውን በቂ አይደለም። አንዳንዴ ለሪፖርት ግብዓት ብቻ ማስታወቂያ ላይ የምናወጣቸው ነገሮች ነበሩ።ሁለት እና ሶስት ተቋም ብቻ ተቀጣ ብለን በዓመት የሆነች ነገር አውጥተን ከሪፖርት አናልፍም ነበር።

እውቅና እና ፈቃድ ከመስጠት ውጪ ቀጣይነት ያለው ክትትል አይካሔድም ነበር። ክትትል ማድረግ አንዱ የተቋሙ ሥራ ነው። በዛ ውስጥ ሰሞኑን እንዳደረግነው ድንገተኛ ግምገማ ማድረግ ነው።ዓመቱን ሙሉ ቁጭ ብሎ አንድ ጊዜ ብቻ የሚካሔድ መሆን የለበትም። በየጊዜው የህብረተሰቡንም ጥቆማ መስማት አለብን። ጥቆማም ባይመጣ ራሱ ተቋሙም ማቀድ አለበት። እንዲህ ዓይነት ሥራዎች አይሠሩም ነበር።

ሌላው የሥርዓት ማነስ ነው።እነዚህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አመሰራረታቸው ራሱ በትክክለኛ አካሔድ ላይ የተመሰረተ አይደለም።ትክክለኛ ከትምህርት ጋር የተገናኘ የሥራ ፈቃድ ራሱ አልነበራቸውም።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ማለት ነው ? የሥራ ፈቃዳቸው ምን ነበር?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ሲቋቋሙ ራሱ የሆነ የችርቻሮ ወይም የጋራዥ ፍቃድ ይዘው የተቋቋሙ ነበሩ።አንድ አካል የትምህርት ሥራ ላይ ለመሳተፍ ከፈለገ በዛ ላይ የተለየ ዕውቀት ሊኖረው ይገባል። የትምህርት ዓይነቱ ራሱ በየትኛው ላይ ይሳተፋል? ለምሳሌ በጤና ወይስ በቢዝነስ የሚለው መለየት አለበት። ነገር ግን እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ ያለው ሁኔታ በምንም ዓይነት ከትምህርት ጋር የማይገናኝ ፈቃድ የነበራቸው ለምሳሌ የአስመጪ እና ላኪ ፈቃድ ይዘው የትምህርት ማስተማሪያ ተቋም ኮሌጅ ይከፍቱ ነበር፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህን ለመዝጋት አትችሉም ነበር?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ተቋሙ ራሱ ባለቤቱ ማን ነው? የሚለውን መጠየቅም አይቻልም ነበር።ዜጋ እየተማረበት ኮሌጅ ተነስቶ ቢጠፋ እንኳ መያዣ እንኳን የለውም ነበር።ሁለት ተቋማት እኮ ጠፍተዋል።ዘመን ሊደርሽፕ ኤንድ ዴቨሎፕመንት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት በሚል ቀበና አካባቢ የተከፈተው ኮሌጅ እና ሴንተራል ጤና ኮሌጅ ተነስተው በቀላሉ ተማሪ በትነው ጠፍተዋል።እስከዚህ ድረስ ቀላል ሆኖ ነበር።

ሌላው እስከ አሁን የተከማቸው የትምህርት ማስረጃ የማጣራት ሥራ እጅግ በጣም ትልቅ ጉዳይ ነው።እጅግ በጣም የተከማቸ እና ውሳኔ የሚያስፈልገው ነው።ብዙ ተጣርቶ ተለይቶ ቁጭ ብሏል። በመቶ ሺህ የሚቆጠር የትምህርት ማስረጃ ተጣርቷል።በዛ ጊዜ ግን ማስረጃ ማጣራት ላይ ይህን ያህል ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ አልነበርም።ለእዚህ አንዱ የአመራር የቁርጠኝነት ችግር ነው።

ሥርዓቱ እያለ ያለመወሰን ችግር ይስተዋል ነበር።የሰው ሃይል እጥረትም ቢኖር በተቻለ አቅም ወስኖ መስራት ያስፈልጋል።እነኚህ ሁሉ ነገሮች የዛኔ ያልተከናወኑ የተጠራቀሙ ሥራዎች ነበሩ። ሌላው ከተቋም ህጋዊነት ጋር ተያይዞ ዞረን አየሠራን ያለነው በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ነው።ድንገተኛ ግምገማ በማድረግ ችግር ያለባቸውን በዙር እየገለፅን ነው።

ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ በህገወጥ ተቋማት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው። በ2011 ዓ.ም ወደ 46 የግል ተቋማት ላይ እርምጃ የተወሰደ ሲሆን፤ በየጊዜው የግል እና የመንግስት ተቋማት የትብብር ስልጠና መስጠት የለበትም ቢባልም አሁንም ድርጊቱን የሚፈፅሙ አሉ። ከኢቢኤች ጋር የገጠመን ችግርም ተመሳሳይ ነው። የከሰስን በውሸት ነው። እውቅናም ሆነ ፍቃድ የለውም።

ከሌሎችም ጋር እየተካሰስን ነው።ድንገተኛ ግምገማ እየተካሔደ ህብረተሰቡም ጥቆማ ሲያመጣ እየተሠራ ነው።በዚህ ዓመት በ2014 ብቻ 305 ካምፓሶች ላይ እርምጃ ወስደናል። በዙር እየገለፅናቸው ነው።አሁን ሶስተኛው ዙር ላይ ነን።

**አዲስ ዘመን፡- የምትወስዱት እርምጃ ምንድን ነው? ተቋሞቹን መዝጋት ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** አይ እንደየደረጃው ነው።ፕሮግራም መዝጋት አለ፤ ካምፓስ መዝጋት አለ፤ አለፍ ሲል ደግሞ ተቋሙን መዝጋትም ይኖራል።ይህ አዲስ አበባ ላይም አለ።

**አዲስ ዘመን፡- በተቋም ደረጃ እንዲዘጋ እርምጃ የሚወሰድበት ወይም የተወሰደበት ምን ያህል ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** መረጃው ገና ይጠራል።ነገር ግን ቢያንስ በአዲስ አበባ ብቻ ሶስት ይሆናሉ።ወደ ፊት እነማን እንደሆኑ እንገልፃለን። እንዲህ አይነት ሥራ በፊት አይሠራም ነበር። ያ የተከማቸ ሥራ አሁን እየተሠራ ነው።ቀደም ብሎ የተነሳው ወደ ስም ቅየራው ለመሔድ እነዚህ የተጠራቀሙ ሥራዎችን ችግር መፍታት አንድ ጉዳይ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ የቆዳ ስፋት እና የሕዝብ ብዛትም ሲታይ በዚህ በአንድ ተቋም ብቻ ሥራውን ስኬታማ ማድረግ አይቻልም።የትምህርት ጥራትን ለመሥራት የሚቋቋም ተቋም ገለልተኛ መሆን አለበት። ይሔ ችግር አሁንም ቀጥሏል። በአዋጅ ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ነው።

በ2011 ዓ.ም የተደረገው በፊት የነበረውን የባለሞያ እጥረት ማለትም ከ15 የማይበልጠውን በተለይ የኢትዮጵያን በሙሉ ጥራት የሚያዩ የጥራት ኦዲት ላይ የሚሰሩ ባለሞያዎች ቁጥር ከ10 የበለጠ አልነበረም። እውነት ለመናገር በዛ ጊዜም መንግስት ባለሞያ እንዳይቀጠር አልከለከለም። ነገር ግን የአመራር ቁርጠኝነት አልነበረም። አሁን ግን የተደረገው የለውጥ አመራሩ ሲመጣ ማለትም ዶክተር አንዱአለም አድማሴ እንደተሾሙ በአንድ ጊዜ ወደ አርባ የሚሆኑ ባለሞያዎች ተቀጥረዋል።

በፊት ተሳስሮ የነበረውን መስፈርት በማቅለል ዜጎች ተቀጥረው ሚናቸውን እንዲወጡ ማለትም ይሔን ያሕል ዩኒቨርስቲ ያስተማረ በሚል ከፍ ያደረጉትን መስፈርት በመቀነስ እና ሲቪል ሰርቪስን በማስፈቀድ በአንድ ጊዜ 42 ባለሞያዎችን መቅጠር ተችሏል።ከዛ በኋላ የሆነው አደረጃጀቱ እንዲህ መሆን የለበትም፤ ብዙ አዳዲስ ክፍሎች ያስፈልጋሉ በመባሉ አደረጃጀቱ ተስተካክሎ ቀርቦ እየተጠየቀ ነው።

አሁን የተሻለ ሁኔታ አለ። ስሙም ከኤጀንሲ ወደ ባለስልጣን ሲቀየር የመቆጣጠር ሃላፊነቱ ይጨምራል። ከዚህም በተጨማሪ በፊት የከፍተኛ ትምህርት እና አግባብነት ኤጀንሲ ነበር። አሁን ግን ትምህርት እና ስልጠና ባለስልጣን ተብሏል። ሃላፊነቱ አሁን ሰፍቷል። በፊት በከፍተኛ ትምህርት ላይ ብቻ ነበር።አሁን ከፍተኛ ትምህርት ብቻ ሳይሆን ቴክኒክና ሞያ እንዲሁም አጠቃላይ ትምህርትን ይመለከታል። ይህንን ሁሉ አጠቃሎ እንዲይዝ የሚመጥነውን ስያሜ ተሰጥቶታል፡፡

በአዲስ መልክ ተቋማት ሲቋቋሙ የሚደረገው መስራት የሚችሉበትን የሰው ሃይል አደረጃጀት እንዲኖር



ፎቶ-ገባቦ ገብሬ

# ተጠየቅ

ከስራ ባህሪያቸው ጋር የተመጣጠነ የሰው ሃይል እና አደረጃጀት እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። አሁን ስለአደረጃጀቱ አስተያየት እየተሰጠበት ነው።እርሱ ሲያልቅ ውጤቱ የሚታይ ይሆናል።እናም ስሙ ሲቀየር ሃላፊነቱ የሰፋ መሆኑን መታወቅ አለበት።

ምክትል ዋና ዳይሬክተር በፊት አንድ ብቻ ነበር፤ አሁን ግን ሶስት ናቸው። ይህ የሆነበት ምክንያት በየዘርፉ እንዲመሩ በማሰብ ነው። ይሄ አደረጃጀቱ ሲያልቅ ይፋ ይሆናል። በዛ መልኩ ሥራቸውን ለመስራት በሚያስችላቸው መልኩ እንዲደራጅ ተደርጓል። የስም ለውጡም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እስኪ ያለፈውን ትተን የአሁኑን እናንሳ። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ተቋሙ ምን ያህል በነፃነት እየሠራ ነው? ቁጥጥር እናድርግ ስትሉ አመራሮቹ ጣልቃ የሚገቡበት ሁኔታ እያጋጠማችሁ አይደለም? እናንተ ራሳችሁ ከአድሉ ምን ያህል የፀዳችሁ ናችሁ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ትክክል ነው። መጀመሪያ ለውጥ የሚመጣው ከውስጥ ነው። በውስጥ በኩል ችግር አለ።ከ2011 በኋላም ካለፈው የቀጠለ የውስጥ ሰራተኞች ሳይቀሩ ከግል ተቋማት ጋር ድርሻ ያላቸው እና የጥቅም ግንኙነት የነበራቸው ነበሩ። በቅድሚያ የተደረገው በግልፅ ቁጭ በማለት ከተቋሙ ሰራተኞች ጋር ውይይት በማካሔድ ችግር መፍታት ተጀምሯል።

በእርግጠኝነት ለመግለፅ ቢያስቸግርም ሌላም አለ።እንደሃሜት በአንዳንድ ኮሌጆች ላይ እርምጃ ላለመውሰድ ሰበቡ ከጀርባ ሰው አላቸው ይባል ነበር። ነገር ግን ከውስጥ ቁርጠኝነት ካለ መስራት ይቻል ነበር።

**አዲስ ዘመን፡- ይህችን ነገር ግልፅ ያድርጉልን፤ ማለትዎ አንድ ተቋም ላይ ከጀርባ ሰው አለ በሚል ሰበብ ተቋም ላይ እርምጃ አይወሰድም ማለትዎ ነው?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** በእርግጥ እንደዚህ ሲደረግ አላየሁም።ነገር ግን እኔ የማውቀው መረጃ እርምጃ ሲወሰድ የትም ቦታ ሔደው ቅሬታ አሰምተው ውሳኔዎችን ያስቀለብሱ ነበር። ለምሳሌ ተጠሪነታችን ለትምህርት ሚኒስቴር ነው። ትምህርት ሚኒስቴር ሄደው ቅሬታ ሲያሰሙ የሚለወጡ ውሳኔዎች ነበሩ። አሁንም ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ግፊቶች አይኖሩም ማለት አይደለም። ነገር ግን ጣልቃ አትግቡብን እያልን በመሆኑ የውጪ ግፊቱ ቀንሷል።

የአሁኑን አመራር ለማሞገስ አይደለም።ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ጣልቃ አትግቡብን በማለት እና በመጋፈጥ እየሠራን ነው። ከዛ ውጪ የገንዘብ አቅም ያላቸው ተቋማት አሉ። ለምሳሌ ኢ. ቢ. ኤች የሚባል አለ። የፍትህ አካላትን እና አመራሮችን በገንዘብ ሊገዛ ይችላል። የሚደግፈው አመራር ሊኖራቸው ይችላል። ነገር ግን ልናጣራ ስንል ዕውቅና እና ፈቃድ እንደሌለው አወቅን። በዚህ ጊዜ ፕሬስ ኮንፈረስ አዘጋጅቶ ሕዝብን ሲያታልል ነበር። ይህ ተቋም በፍርድ ቤት ከመክሰስ አልፎ ካሳ እስከ መጠየቅ ደርሷል። ለእዚህ ድፍረቱ አመራር ከጀርባ ስላለው ሊሆን ይችላል።

ይህ ድርጅት ከውጪ የመጣ መንግስታዊ ያልሆነ የእርዳታ ድርጅት ነው። ከጅማ ዩኒቨርስቲ ጋር የትብብር ስልጠና ይሰጣሉ። ለዚህ ፈቃድ የላቸውም።ጅማ ዩኒቨርስቲ የሚሠራው በመንግስት በጀት ነው።ነገር ግን ይህ ተቋም አብሮ ሲሠራ የሚጠቀሙት በጀት እንዴት እና በማን ነው? የሚለው ያጠያይቃል። ይሔ ሳይታይ ስልጠና አትስጡ ተብለው ተከልክለው ነበር። እንዴት ተከለከልን ብለው መጥተው ለማስፈራራት ሞከሩ።

እነዚህ አካላት ከጀርባ ሰው አላቸው።እኔም በእነርሱ ዙሪያ መረጃ እንዳልሰጥ ተከልክዬ ነበር።ወደ ተቋማችን የበላይ ሀላፊ በመደወል እኔም መረጃዎችን እንዳልሰጥ ተደርጎ ነበር። አመራሩ ቁርጠኛ ስለነበር ‹‹እኔን ጠይቁኝ›› ብሎ መረጃውን እንድለቅ ተፈቅዶልኛል። አቅጣጫ የሰጠውና ያንን መልዕክት የላከ አመራር ነበር። በአመራሮች ተመክተው መመሪያን የሚጥሱ መኖራቸው አይካድም።

**አዲስ ዘመን፡- ስለዚህ አመራሮች ጣልቃ ለመግባት የሚሞክሩበት ሁኔታ ቢኖርም እናንተ ግን ተፅዕኖውን ተቋቁማችሁ እየሠራችሁ ነው ማለት ይቻላል?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ቁርጠኝነት ያልኩት ይሔንን ነው።ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ ተከሰናል፤ ብዙ ታግለናል።ለማንም ወደ ኋላ አላልንም።አንዱ ችግር ደግሞ የፍትሕ አካላት የሚፈጥሩት ነው።እውነት ለመናገር ምክንያታቸው ምን እንደሆነ አይታወቅም፤ ወይ በገንዘብ ተታለዋል፤ አልያም ጥቅም የሚገኙበት ሁኔታ አለ።ውሳኔ ቶሎ አይሰጡም።አንዳንድ ውሳኔያቸው አድሏዊ ነው።ብዙ ተጨባጭ መረጃዎችም ቀርበው ፍትሐዊ ውሳኔዎች እየተሰጡ አይደለም።



**አዲስ አበባ ላይ 106 ተቋማት ከማስጠንቀቂያ እስከ ተቋም መዝጋት እርምጃ የተወሰደባቸው አሉ**

የአገራችን የፍትህ አካላትን በሚመለከት እንግለፅ ካልን ብዙ ተጨባጭ መረጃዎች ቀርበው ፍትሃዊ ውሳኔ እየተሰጠ አይደለም። ሕግ ጥሶ ከመስሪያ ቤቱ ጋር ተካሰን ውሳኔው አንድ መቶ ብር ብቻ መሆኑ አስገራሚ ነው።እንደዚህ ዓይነት በጣም ማሾፍ የሚመስሉ የፍርድ ውሳኔዎች አሉ። ሌሎች ደግሞ ብዙ እስከ አሁን ውሳኔ ያልተላለፈባቸው አሉ። ነገር ግን የፍትሕ አካላቱ ቢያግዙንም ሆነ በወቅቱ ምላሽ ቢሰጡ ሁሉም ተቋማት ምላሽ ይሰጡን ነበር።

በሌላ በኩል ደግሞ በእርግጥ አመራሮችን ተመክተው መስሪያ ቤቱ የሚያስተላልፋቸውን ውሳኔዎች ላለመቀበል የሚያንገራግሩ ተቋማት አሉ። በተጨማሪ በውስጥ በኩል ያለው ችግር ሲታይ ድርሻ ነበራቸው የሚባሉ የነበሩት አምስት አካባቢ የሚሆኑት ባለሞያዎች ለቀዋል።አሁን ሙሉ ለሙሉ ጠርቷል ማለት አይቻልም። ይህን ስል አሁን ድርሻ ያላቸው አሉ ለማለት አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- ከሳይ ወደ 300 የሚደርሱ ተቋማት ላይ እርምጃ እንወስዳለን ብላችኋል።እንዴት ይህ ሁሉ ተቋም እስከ አሁን ሲሠራ ቆየ? ለምን በፊት ከሥር ከሥር እርምጃ አልተወሰደም?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ከላይ እንደገለፅኩት የተከማቸ ችግር ነበር።አንደኛው የተቋማችን የራሱ የአመራር ቁርጠኝነት ማነስ ሲሆን፤ ሌላው ሥራዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ ካለመሰራታቸው ባሻገር የሰው ሃይል ችግርም ነበር። ስለዚህ በፊት በአግባቡ ያልተሠራ የተጠራቀመ ችግር ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ እየተሠራ ነው። ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ አመራሮች ቁጭ ብለው ተወያይተው ወደ ሥራ ገብተዋል። ነገር ግን ከተቋማትም ጋር መደጋገፍ የለም።

ተጠሪ ተቋም እንደዋና መስሪያ ቤት መደገፍ ባለበት ልክ እየደገፈ አይደለም። ከሪፖርት ግምገማ ባለፈ ሕገወጥ ተቋማት ሲበዙ እና ሲያስቸግሩ ድጋፍ በሚያስፈልግበት ሰዓት መስሪያቤቱን እያገዙት አልነበረም።አሁን የሌለው የሳይንስ እና ከፍተኛ ተቋማት ሚኒስቴር ሲቋቋም በወቅቱ የነበሩ አመራሮች ጥሩ ሠርተዋል።ሰራተኛውን አግኝተው ከአመራሩ ጋር ያለው ችግር ምንድን ነው? ብለው ተወያይተው ተደጋግፈዋል። የወቅቱ ሚኒስትር ፕሮፌሰር ሒሩት ወልደማርያም በሰፊው ድጋፍ ሲያደርጉ ነበር።

ቁጭ ብለን ከተወያየን በኋላ አዲስ አበባ እና በአዲስ አበባ ዙሪያ ድንገተኛ ምርመራ በማድረግ በ2011 ዓ.ም ወደ 46 ሕገ ወጥ ተቋማት ተገኙ። እነዚህን ከ2011 በፊት ቀድሞ ማስቆም ይቻል ነበር። የመንግስት ተቋማትንም ክትትል በማድረግ እርምጃ ተወስዷል። ውሳኔዎች ተሰጥተዋል። አንዳንድ ክልከላዎች ተደርገዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የመንግስት ተቋማት ላይ ምን ያህል እርምጃ ወሰዳችሁ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** የመንግስት ተቋም ዙሪያ በ2012 ዓ.ም አካባቢ የትብብር ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት ነበሩ።የግል ተቋማት ከመንግስት ተቋማት ጋር በትብብር ስልጠና መስጠት አይቻልም፤ ተብሎ የተከለከለውን ማስተግበር ተችሏል። መመሪያው የወጣው በ2006 ዓ.ም ነበር።ነገር ግን መተግበር የተጀመረው በ2012 አካባቢ ነው።እዛ ላይ በዝርዝር ቢታይ አብረው በትብብር መስራታቸው ብዙ ችግር ነበረበት።ከዚህ ባለፈ አዋጁን ለማስተግበር ብዙ ሠርተናል ለማለት እቸገራለሁ፤ ብዙ ይቀረናል።

ቀጥሎ ለምን አሁን 300ዎቹ ላይ እርምጃ ተወሰደ? ለሚለው በ2014 ዓ.ም በስፋት የተሠራው በፊትም ሲታቀድ የነበረ ሥራ ነው። ወደ 82 የሚሆኑ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው ናቸው። አዲስ አበባ ላይ 106 ተቋማት ከማስጠንቀቂያ እስከ ተቋም መዝጋት እርምጃ የተወሰደባቸው አሉ። ፕሮግራም የተዘጋባቸው፣ ካምፓስ የተዘጋባቸው ወይም ተቋም የተዘጋባቸው አሉ።በክልል በመጀመሪያ ዙር ወደ 95 ተቋማት ይፋ አድርገናል። በመቀጠል 104 ተቋማትን ይፋ አድርገናል። 300 ካምፓሶች ላይ እርምጃ ተወስዷል።

ይህ እርምጃ ሲወሰድ ተጠራቅሞ የመጣ በፊት የተለመደ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ምን ያህል ህገወጥ የትምህርት ማስረጃ ሊኖር እንደሚችል መገመት ከባድ ነው።ሌላው የአደረጃጀት ችግር ነው።ተቋሙ መስራት በሚችልበት መልኩ እንዲደራጅ ብዙ ጊዜ ጥያቄ ቀርቧል። ሚኒስቴር መስሪያቤቱም ተገቢውን ድጋፍ አልሰጠም። የሚመለከታቸው አካላትም አልወሰኑበትም።ስለዚህ እየተጓተተ መጥቶ፤ አሁን ትኩረት ተሰጥቶት የተሻለ ሁኔታ እየተፈጠረ ነው።

በ2011 ዓ.ም ላይ እኛ ጋር መረጃ ያለው 75ሺህ ተመራቂ እና ተማሪ ብቻ ነበር። ተቋማቱን የምታስተምሩትን እና ያስተማራችሁትን ተማሪ መረጃ አምጡ ብለን ማስገደድን ማንም አልከለከለም። ይህም የውስጥ የራሳችን ችግር ነው።አሁን ግን በአራት ዓመት ውስጥ አንድ ነጥብ አንድ ሚሊየን መረጃ ተሰብስቧል፤ አሁንም ገና ነው።አሁን የከፍተኛ ትምህርት መረጃ አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቷል። እዛው ሆነው በተቋማቸው ቶሎ መረጃ እንዲያስገቡ ይደረጋል። ሌላው ከዚህ በፊት ያልነበረው የኦን ላይን ትምህርት መመሪያ ኢትዮጵያ ውስጥ አልነበረም። አሁን ግን መመሪያ ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

በተጨማሪ የግል ተቋማት ራሳቸው ተሳትፈው ያፀደቁት የሥነ ስርዓት መመሪያ አለ።እርሱ ነገር ሲጓተት መጥቶ አሁን ገና ተግባር ላይ ይውላል።በፊት አንድ ተቋም ምን ሲያጠፋ ምን ይቀጣ? የሚለው ግልፅ አልነበረም። ይህም የተጀመረው ቆይቷል። ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገው ግን አሁን ነው። ይሔ በፊት ምን ያህል ብዙ ችግር እንደነበረና ምን ያህል እንዳልተሰራበት ያሳያል።

ከ2011 ጀምሮ ከተጨመረው የተወሰነ ባለሞያ ውጪ አሁንም ገና አደረጃጀቱ አልተቀየረም።ደመወዝ አከፋፈሉም ተመሳሳይ ነው፡፡ ሆኖም ባለን ዓቅም ብዙ ነገር እየሠራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን የትምህርት ጥራት ላይ እየሠራን ነው ብትሉም ዛሬም ችግሩ አልተቀረፈም።ማሳያው አንዱ ሲኦሲን የሚያልፈው ቁጥር ውስን መሆኑ ነው።ሲ ኦ ሲን በተመለከተ ምን ይላሉ?**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ሲኦሲ 2003 እና 2004 አካባቢ የተጀመረ ነው። ሲጀመር ጥራትንም ለማረጋገጥ ነው። የኛ ተቋም ዲግሪ ለመማር ማለትም ከቴክኒክ እና ሙያ የተመረቁ ሌቭል 4 ሲኦሲ ማለፋቸውን ያረጋግጣል።አንዱ ድንገተኛ ግምገማ ሲደረግ የተማሪዎች ፋይል በድንገት ሲታይ፤ በዚህ ዙሪያ ሰፊ ችግር መኖሩ ታይቷል። ተማሪው ራሱ ከተቋሙ ጋር ተስማምቶ ማሟላት ያለበትን መስፈርት በቀጣይ አሟላለሁ ብሎ ቃል ገብቶ እንደሱቅ ዱቤ ሌላ ጊዜ እናመጣለን ብለው ስምምነት ተፈራርመው የሚማሩ እና የሚያስተምሩ መኖራቸው ታውቋል።

ተቋሙ በዚህ ምክንያት ለሚደርስ ኪሳራ ሃላፊነቱን ላለመውሰድ ተማሪን ያስፈርማል። ተቋሙ ብቻ ሳይሆን ዜጋውም ወደ ስህተት ይገባል። ከሲኦሲ ጋር በተያያዘ ብዙ ተቋማት ችግር ውስጥ የሚሆኑበት ሁኔታ አለ።ብዙ ተመራቂዎች እስከ ላይ አመራርም ድረስ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ተቋሙ በትክክል ሀላፊነቱን ቢወጣ የጥራት ችግር ይህን ያህል የተወሳሰበ አይሆንም ነበር የሚሉ አሉ ለዚህ ምን መልስ አላችሁ።**

**አቶ ታረቀኝ፡-** ሲኦሲውም አንዱ የጥራት ማስጠበቂያ መንገድ እኮ ነው።ሲኦሲውን እንዲያልፉላቸው ተማሪዎቻቸውን ያበቃሉ።ይሔም አንዱ መንገድ ነው። የእኛ ሚና ጥራትን ከማስጠበቅ አኳያ የጥራት ኦዲት የሚባል አለ።ነገር ግን ተቋማት የሚሰጣቸውን ግብረመልስ ተግባራዊ ባያደርጉ ቅጣት የለውም። ራሳቸውን እንዲቀይሩ ምክር ብቻ ይሰጣል። ክትትል ብቻ ይደረጋል።

አሁን የጥራት ኦዲት ራሱ አስገዳጅ እንዲሆን እየተሠራ ነው።እዚህ ላይ ድክመት አለ።አደረጃጀቱ ይህንን ሊያሰራ በሚችል መልኩ ይሆናል። ሌላው ውሳኔዎች እንዳይቀለበሱ ይሠራል።በእርግጥ የተጠሪነት ጉዳይም አንድ ነገር ነው። ተቋሙ በዚህ መልኩ በአዋጅ ስለተቋቋመ እርሱን መንካት አንችልም።

**አዲስ ዘመን፡- ስለነበረን ቆይታ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ።**

**አቶ ታረቀኝ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## "ዘመን በዘመን አይዋጅም"

እያንዳንዱ ዘመን ትቶት የሚያልፈው የራሱ አሻራ አለው።የትናንቱ ዘመን "እንደ ፈሰሰ ውሃ ላይታፈስ" ታሪክ ሠርቶም ይሁን የተሠራውን አበላሽቶ በትረ ሥልጣኑን ለዛሬ አስረክቦ እብስ ብሎ ተሰናብቷል።ጸጸት፣ ቁጭትና ትዝታ "የተገጠመላቸው ዐይን" የሚመለከተው ትናንትንና የኋላውን ብቻ ሲሆን፤ ተስፋ ደግሞ ትኩር ብሎ "እርምጃውን እያፋጠነ የሚገሰግሰው" በዛሬ ላይ እየተረማመደ ወደ ነገ መዳረሻው ነው።

እያንዳንዱ ግለሰብም የሚኖርበትን ዘመን ይዋጅ ካልሆነ በስተቀር ወደ ኋላው ተዘርግቶም ይሁን ተንጠራርቶ የኃላፊውን ጊዜ አስገብሮ ከፉም ይሁን ደግ አሻራውን ለማሳረፍ ሰብዓዊ ባህርይውም ሆነ አቅሙ አይፈቅድለትም።ባዕዳን ባለብሂሎች "አንድን ወራጅ ወንዝ ሁለቴ አታቋርጠውም" የሚሉት ፈሊጥ አላቸው።ባለቅኔው የክብር ዶ/ር ከበደ ሚካኤል "አዝማሪና የውሃ ሙላት" በሚለው ተወዳጅ ግጥማቸው፡-

**"እስኪ ተመለከተው ይህ አወራረድ፣**
**ያልሰማው ሲመጣ የሰማው ሲሄድ፤**
**ድምጡን እያውካካ መገሥገሡን ትቶ፣**
**ማን ይሰማኝ ብልህ ትደክማለህ ከቶ፡፡"**

በማለት በግጥማቸው ያስታወሱን ይህንኑ የወንዝ አወራረድ "ተአምራዊ" እውነታ ነው።ዘመንም እንደዚያው ሂያጅ እንጂ ደርሶ ተመላሽ መንገደኛ አይደለም።ቢዘፍኑለትም፣ ቢዘምሩለትም ሆነ ቢዘይሩለት ዘመን እንደ ወንዝ ነው።ሲሄድ ውሎ ሲሄድ የሚያድር፡፡

ሞኝ ሰው አካሉን ዛሬ ላይ አቁሞ፤ ትዝታውን ትናንት ላይ ቸክሎ ሲያብሰለስል፤ ብልህ ሰው ግን ዛሬውን ሊያደምቅ፣ ነገውን ሊያስውብ ይተጋል።"ዘመናችሁን ዋጁት እንጂ ሞኞች አትሁኑ" የሚለው የቅዱስ መጽሐፍ መሪ ጥቅስ ለዚህ ጽሑፍ ማኀልበቻነት ቢጠቀስ ተገቢ ይመስለናል፡፡

እርግጥ ነው ትናንትን በትዝታ መናፈቅ፣ የታለፈውን መልካምም ይሁን አስከፊ ጊዜ እያስታወሱ እንደ ድምጸ መረዋው ዘሜኛ "እህህ" እያሉ መብሰልሰል ሰብዓዊ ተፈጥሯችን እንደሆነ አይካድም።"ያሳለፍነው ዘመን" እየተባለ ቢወደስ ወይንም ቢወቀስ ከአግባብ ማፈንገጥ ተደርጎ ሊታሰብ አይገባም - ምክንያቱም ትዝታ ስለማያረጅ።

"የከሰረ ዐረብ አርጅቶ ከጃጀ በኋላ በወጣትነት ዘመኑ ዱቤ የሰጣቸውን ደንበኞቹን ስም ለመፈለግ አሮጌ መዝገቡን ያገላብጣል" እንዲሉ፤ ትናንትን ረትቶ ለመጣል ግብ ግብ ካልፈጠርኩ ብሎ ወላንሶ በመግጠም ለያዥ ለገራዥ ማስቸገር የአእምሮ ጤንነትን ያጠራጥራል። ቢሞከርስ መች ይቻላል፡፡

ከትናንት ማህደር ውስጥ ታሪክን፣ ተሞክሮን ወይንም ጥፋትን እየመዘዙ "እንዲህ ቢሆን ኖሮ ወይንም እንዲህ በመሆኑ እንዲህ ሆነ ..." እየተባለ በትምህርትነቱ መጥቀስም ሆነ መተቸት ይቻል ይሆናል።በየዘመኑ "አጥፊ" ተሰኝተው ትውልድን የበደሉ ግለሰቦችን፣ ቡድኖችንና ሥርዓቶችን በአግባቡ መሄስና መሞገቱ ክፋት የለበትም።ነገር ግን ሞቶ የተቀበረን፣ ተንኮታኩቶ የተሰባበረውን ፍልስፍናና ርዕዮተ ዓለምን በዛሬ ጀንበር እንደ አዲስ በማስተዋወቅ "ተጋግዘን ካላላመጥንና ካላመነዠክት" ብሎ ማስገደዱም ሆነ ማባበሉ "ለራስ አባት ቅድመ አያት ካልሆንኩ" ብሎ የመሟገት ያህል ዋዘኛነት ነው።

ነፍሱ ሄሩ የሥነ ጽሐፍ መምህራችን ደበበ ሰይፉ

> **በአሸባሪነት የተፈረጁት የዛሬዎቹ "የዘመን ጠበኛ" ቡድኖች ተወልደው እትብታቸው የተቀበረው በዚያው በጠቀስነው ዘመን ጫካ ውስጥ እንደነበር የታወቀ ታሪካቸው ነው።**

እነዚህን መሰል ከዘመናቸው ጋር የተኳረፉ የሃሳብ ምንዱባን የገለጻቸው እንዲህ በማለት ነበር፤ "እናንቴ የአባቶቻችሁ ልጆች፤ የአያቶቻችሁ ቅድመ አያቶች" - ግሩም ገለጻ ነው፡

ይሄው የሥነ ጽሑፍ ጎምቱ ባለሙያ መክነፍ እንጂ መስከን ባህርይው ያልሆነውን የጊዜን ዑደት በተባ ብዕሩ የሸነቆጠው እንዲህ በማለት ነው፡፡

**ጊዜ በረርክ በረርክ፣**
**ጊዜ በረርክ በረርክ፣**
**ግን ምን አተረፍክ**
**ግን ምን አጎደልክ፣**
**ሞትን አሳሸነፍክ፣**
**ሕይወትን አልገደልክ፡፡**

ዘመን እየከነፈ የሚበረውና የሚጋልበው ከሕይወታችን ላይ ቀናችንንና እድሜያችንን እየቆነጠረ ነው።"ኤዲፐስ ንጉሡ" በሚሰኘው ጥንታዊ የግሪኮች ተውኔት ላይ የሰው ልጅ ዕድሜ የተመሳጠረው በሚከተለው የዕንቆቅልሽ ፍልስፍና ነው።"ጠዋት ላይ በአራት እግሩ የሚሄድ፣ ከሰዓት በሁለት እግሩ የሚራመድ፣ ምሽት ላይ በሦስት እግሩ የሚውተረተር ምንድን ነው?"

መልሱ ያው "ሰው ነው" የሚል ሲሆን፤ ዕንቆቅልሹ ሲፈታ የምሥጢሩ ይዘት የሚከተለውን ይመስላል።"በጠዋት የተመሰለው የአራት እግር እርምጃ ተምሳሌቱ የሕጻንነትን የመዳህ ዘመን የሚያስታውስ ሲሆን፣ የጠዋቱ የሁለት እግር ጉዞ ደግሞ አፍለኛውንና ቢሮጡ የማይደከምበትን የዘመነ ወጣትነት ዕድሜ ያመላክተናል።የዘመነ-ሽበት የእርጅና ወቅት የተነጻጸረው ደግሞ ምርኩዝ ከመጨበጥ ጋር ነው፡፡"

ከዘመን ጋር የማይለወጥ ምናልባትም የተራራ ላይ ቋጥኝ ድንጋይ ሊሆን ይችላል።ገፋ አድርግን ብንመረምር ሌላ የተሻለ ገላጭ ምሳሌ ሊጠፋ እንደማይችል ይገባናል።የድንጋይ ነገር ከተነሳ አይቀር በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተፈጸመ የሚባልን አንድ ሁኔታ አስታውሰን እንለፍ።በመንገድ ሥራ ላይ የተሰማራ አንድ የኮንስትራክሽ ድርጅት የተራራ ሥር መሹዋለኪያ ለመሥራት በግሬደሩና በመከስከሻዎቹ ግዙፍ ማሽኖቹ አማካይነት ቋጥኙን ድንጋይ እየፈረካከሰና እየከሰከሰ የመንገድ ንጣፉን ሥራ ሲከውን የተመለከቱ የዚያ አካባቢ ተረበኞች እንዲህ በማለት ገጠሙ ይባላል፡፡

**"ድንጋይ አይሞት ያሉት ሞት ተፈረደበት፣**
**እየከሰከሱ መኪና ነዱበት፡፡**

ይሄን ብለው ብቻ ቢያበቁ ደግ፤ በመቀባበልም እንዲህ በማለት ትዝብታቸውን ገለጹ ተብሎ ይነገራል፡፡

**"እስቲ በል ተቦካ፣ እስቲ በል ተፈጨው**
**እስቲ በል ትጋገር፣**
**አንተም ስንፍናውን አብዝተኸው ነበር፡፡**

እያንዳንዱ ትውልድ የራሱን ዘመን ዋጅቶ ያስገብር ካልሆነ በስተቀር ወደ ትናንት ተንጠራርቶ "በአደረ አፋሽነት ባለቤት" መሟገት ፋይዳ እንደሌለው ደጋግመን ለማሳየት ሞክረናል።ለዚህ አገላለጻችን በጥሩ አብነት የሚጠቀሰው የሀገራችን ፖለቲካና ተዋናዮች ናቸው።እንዴታው ተደጋግሞ ስለተገለጸ በአጭሩ እናስታውስ፡፡

የ1960ዎቹ የሀገራችን ለውጥ አላሚ ወጣት ፖለቲከኞችን በጥቂት ቃላት እንግለጻቸው ከተባለ "የጥራኝ ጫካው፣ ጥራኝ ዱሩ ናፋቂና አንጎራጓሪዎች" እና "የአስተሳሰብ ግትሮች" ነበሩ ብሎ መደምደሙ "ሃሰት" አያሰኝም፡፡

በአሸባሪነት የተፈረጁት የዛሬዎቹ "የዘመን ጠበኛ" ቡድኖች ተወልደው እትብታቸው የተቀበረው በዚያው በጠቀስነው ዘመን ጫካ ውስጥ እንደነበር የታወቀ ታሪካቸው ነው። ቡድናቸውን ያደራጁትና ያፈረጠሙትም በውይይት፣ በመተማመን፣ በመግባባትና በመቀባበል ሳይሆን እርስ በእርስ ደም እየተቃቡና፣ የተረፉትም እንደ አሜባ እየተበጣጠሱና እርስ በእርስ እየተበላሉ አንዱ አንዱን በመዋጥ ነበር፡፡

ማደሪያቸው ጫካ ነበር ቢባልም እንኳን (ጫካው ምናልባትም የከተማ መሸሸጊያቸውም ሊሆን ይችላል) ከተሸሸጉበት ዱር ይወጡ የነበረው አንድም መንግሥታዊ ተቋማትን ለማውደም አለያም "ጠላት ያሉትን የደመኛቸውን" ሕይወት ለመቅጠፍ እንደነበር ያልመሸበት ታሪካቸው ምስክር ነው፡፡

የእነዚሁ ቡድኖች ቅሬታዎችና የእነርሱ ውላጆች የሆኑት ከግማሽ ክፍለ ዘመን በኋላ ዛሬም ድረስ በቆሙበት እንደተቸከሉ እንጂ ከዘመን ጋር ተለውጠው መቼ አየናቸው? እንኳንስ ርዕዮተ ዓለማቸው በቋንቋ አጠቃቀማቸው እንኳን ሳይቀር አንደበታቸውን ሲገሩ መች ተመለከትናቸው? የኤዲፐስን ዕንቆቅልሽ ደግመን እናስታውስና እነዚህ "የዘመን ኩርፈኞች" የምርኩዝ ዘመናቸውን ነጭ ሽበት እያረከሱ ወደ አራት እግራማነት የዳዴ ዘመን ካልተመለስን ብለው ከዘመንና ከትውልድ ጋር ሲሟገቱ ስለምን ኅሊናቸው እንደማይገስጻቸው አይገባንም።

ዕድሜና የሕይወት ተሞክሮስ እንዴት አይመክራቸውም? "ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ አስብ ነበር፤ ጎልማሳ ስሆን ግን የልጅነት ጠባዬን ሽሬያለሁ" እንዳለው ቅዱስ ጳውሎስ፤ እንደምን ከእውነታ ጋር መታረቅ አቃታቸው? "ድንጋይ አይሞት አሉ" ባዮቹን ሰሜንኞች ደግመን ብናስታውስ አባባሉ በሚገባ ይገልጻቸዋል።

ከአርባ ዓመት በፊት ይቀናቀኑት ከነበረው ሥርዓት ጋር በጠረጴዛ ዙሪያ ተደማምጠና ተደራድሮ መግባባት ስለተሳናቸው በዚያኛውም ወገን ሆነ በእነርሱ በኩል የሆነውን ሁሉ በሚገባ እናስታውሳለን።"ጦርነት ስለማይበጃችሁ ችግራችሁን በሰላምና በድርድር ፍቱ፤ ቆመንለታል ለምትሉት ሕዝብና ሀገር ስትሉም በመካከላችሁ መቀራረብ ተፈጥሮ ተነጋገሩ" በማለት ዛሬም እንደ ትናንቱ ድምጻቱ እንኳን ሳይለይ በርካታ የዓለም መንግሥታት ምክር እየሰጡ ይገኛሉ።እንዴት ኅሊና አለኝ የሚል የግለሰቦች ስብስብ ቆም ብሎ ነገሮችን ግራና ቀኝ በማየት በሰላማዊ መንገድ ለመነጋገር ማሰቢያው ሊደፈን ልቡም ሊደነድን ቻለ?

እንደ ኢትዮጵያ ፖለቲካ ለራሱም ግራ ተጋብቶ ለተቀረው ዓለምም ግራ የሆነ ፖለቲካ ስለ መኖሩ እርግጠኛ መሆን ያዳግታል።ዛሬም እንደ ትናንቱ "ጥራኝ ጫካው፤ ጥራኝ ዱሩ፤ ላንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ" እያሉ የሚያቅራሩና "በተመሳሳይ ቅኝት ከበሮ እየደለቁ" ሃምሳ ዓመት ሙሉ በደም ጥማት ሱስ እንዳፋሹኩ ግራ ተጋብተው ግራ ያጋቡ ብጤ "የዘመን ጠበኞች" በሌሎች ሀገራት ይኖሩ ከሆነ የሚያውቁ ቢያሳውቁን አይከፋም፡፡

**"ወደ ኋላ ሄደህ በሃሳብ ከማለም**
**ቀኑ እንዳይመሽብህ ትናንት ዛሬ አይደለም፡፡"**

እንዲሉ፤ "ገዳይ ደሞ" ዜማን እያቀነቀኑ ንጹሐንን በመፍጀትና ንብረት እያወደሙ ወደ ሥልጣን ለመምጣት መቃዠት የማያዋጣ ብቻም ሳይሆን እብደትም ጭምር መሆኑን እነ አልሰሜ ቢሰሙ ይበጃቸዋል፡፡

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ እንደ ትናንትናው በመሪዎቿ ግትርነት "የፈለገው ዋጋ ይከፈላል እንጂ ወሳኙ ሻምላዬ ነው" ብላ ለመፋለም ፍላጎቱም ሆነ እምነቱ በጭራሽ የላትም።ሰላማዊ ጥሪዋ "ኑና እንዋቀስ" የሚል ነው።መልእክቱ እየተስተጋባ ያለው ደግሞ ሀገራዊ የምክክሩን ወንበር እያበጃጀ ባለው "ብሔራዊ ኮሚሽን" አማካይነት ነው፡፡

ባረጀና ባፈጀ "የተባይ መፈልፈያ" የርእዮተ ዓለም ካፖርት ራሳቸውን የጀቦኑ ተቸካዮችም ሆኑ "ጫካ ውስጥ መሽገው" የንጹሐንን ደም ለማፍሰስ ሰይጣን የተጠናወታቸው "ዘመን አምካኝ" ቡድኖች ወደ ቀልባቸውና ወደ ኅሊናቸው ተመልሰው እንደ ሰብዓዊ ፍጡር "ከእብሪት እንቅልፋቸው ባንነው" ወደ ሰላም ቢመለሱ ይበጃቸዋል።

"ይሄን ያህል ሞተ! ይሄን ያህል ተደመሰሰ!" ቢቸግርና ግድ ቢሆን እንጂ "ሰላምን የሚተካ" ግብ ሊሆን በፍጹም አይችልም።ዘመን የሚዋጀው በዘመነኛው ትውልድ እንጂ፤ ዘመን ከዘመን ተስማምቶ ለመቀባበል ባህርይው አይፈቅድም።ስለዚህ እያንዳንዱ ማለዳ የአዲስ ዘመን መባቻ እንጂ የአሮጌ አስተሳሰብ ኮሮጆ ስላልሆነ "እነ ዘረፌዋ" ወደ ኅሊናቸው ተመልሰው ለሰላም ቢዘምሩ ይሻላቸዋል።ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

## ወጪ ገቢ ንግድን ያሳልጣል የተባለው ነጻ የንግድ ቀጠና

**ፍሬሕይወት አወቀ**

ከሰሞኑ የበርሃ ገነት በመባል በምትታወቀው ድሬዳዋ ከተማ የኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የነጻ ንግድ ቀጠና ተቋቁሟል። በነጻ የንግድ ቀጠና ውስጥ የሚገኙ አምራች ፋብሪካዎች ለምርት አገልግሎት የሚጠቀሟቸውን ግብዓቶች ያለምንም ቀረጥ፣ የኮታ ገደብ፣ የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ... ወዘተ ከውጭ አገራት እንዲያስገቡ የሚፈቅድ አሰራር እንደሚኖር መረጃዎች ያመላክታሉ።

የነጻ ንግድ ቀጠናው መከፈት ዓላማዎች፤ የውጭ ምንዛሬ ግኝትን ማሳደግ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት (FDI) መሳብ፣ የኢኮኖሚ መነቃቃትን በማምጣት የሥራ ዕድል መፍጠር፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት አንድ ውጤት የሆነውን የቴክኖሎጂ ሽግግር ለማስገኘት፣ በከፍተኛ ወጭ ተገንብተው በቂ አምራች መሳብ ያልቻሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ወደ ሥራ ማስገባት ናቸው።

የነጻ ንግድ ቀጠና ዞን አይነቶች ከአገር አገር የሚለያዩ ሲሆን፤ በዋነኛነት በሦስት መሠረታዊ ዘርፎች ላይ ትኩረት ተደርጎ የሚሠራበት ነው። የመጀመሪያው የአምራች ዘርፉን ይመለከታል፤ ይህም ለአገር ውስጥ ገበያ የሚያመርት ወይም ከተመረተ በኋላ ኤክስፖርት የሚያደርገው ነው።

ሁለተኛው በአስመጪና ላኪ ድርጅቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል፤ ይሄ ደግሞ ጥሬ ዕቃና አላቂ ዕቃ አስመጪዎች ወደ አገር ውስጥ ዕቃዎችን በማምጣት በቀጣናው ውስጥ የሚያከማቹበት፣ የሚያቀናብሩበት እንዲሁም መልሰው ወደ ውጭ አገሮች የመላክ ሥራዎች የሚያከናውኑበት ነው። እንዲሁም ሂደቱን ለማሳለጥ ቀልጣፋ የሆነ የሎጂስቲክስ አገልግሎት የሚሰጥበትም ነው።

ከእነዚህ በተጨማሪም በቀጣናው የሚሰጠውን አገልግሎቶች የሚያቀላጥፉ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ የደረቅ ጭነትና የምክር አገልግሎቶች በቅንጅት ይሰጥበታል፡፡

በነፃ የንግድ ቀጣናው የአገሪቱ የጉምሩክ ሥርዓትና አጠቃላይ ሕጎች ልማቱን ለማሳለጥ በሚያስችል ሁኔታ ላልተው የሚተገበሩበት ነው፤ በዚህ ነፃ የንግድ ቀጣና ውስጥ ገብተው የሚሠሩ ባለሀብቶች፣ አስመጪና ላኪዎችም ሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች የልዩ ልዩ ማበረታቻዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

ነፃ የንግድ ቀጠና ውስጥ የሚገቡ አምራቾች ከነፃ የንግድ ቀጠናው ሳይወጡ የምርት ግብአቶችን ማግኘት የሚያስችላቸውም ይሆናል። ከነፃ የንግድ ቀጠናው ውጪ የሚያመርቱ ኩባንያዎች በግብዓትነት የሚጠቀሟቸውን ያላለቁ ምርቶች ከውጭ ሲያስገቡ እንዲከፍሉ የሚጠበቅባቸው ቀረጥና ታክስ በነፃ ንግድ ቀጠና ውስጥ ተግባራዊ የማይደረግ በመሆኑ የምርት ወጪ የሚቀነስ ነው።

ይህም የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አምራቾች ወደ ኢትዮጵያ ነፃ የንግድ ቀጣና እንዲገቡ ትልቅ ብርታት የሚሰጥ እንደሚሆን ይታሰባል። በመሆኑም ነፃ የንግድ ቀጣና መቋቋም የሥራ ዕድል የሚፈጥር ሲሆን፣ ከዚያው ጎን ለጎንም የውጭ ምንዛሬ፣ የኤክስፖርት ዕድገት፣ የኤክስፖርት ምርት ስብጥር ከማሳደግ በሻገር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ረገድ የሚጫወተው ሚና በትልቁ የሚነሳ መሆኑ ይብራራል፡፡

የመንግሥት ገቢ በማሳደግ ረገድም የራሱን ጉልህ ሚና የሚጫወት ይሆናል የሚባለው የነፃ ንግድ ቀጣና እንቅስቃሴ፣ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና የሠራተኞች ክህሎትን ለማሳደግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል። በተጨማሪም የነፃ ንግድ ቀጣናው የሚመሠረትበት አካባቢን ወይም ቀጣናን በማልማትና በማሳደግ ረገድ የሚኖረው አበርክቶ ጉልህ መሆኑም ይገለጻል፡፡

በንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር የብሔራዊ ጥራት መሰረተ ልማት ማረጋገጫ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ እንዳለው መኮንን ነጻ የንግድ ቀጠናን አስመልክተው እንዳሉት፤ ነጻ የንግድ ቀጠና ማለት በአገሪቱ ያሉ ወይም ደግሞ ከዚህ ቀደም ሲሰራባቸው የነበሩ የንግድ ህጎች የማይመለከተው ሆኖ ለብቻው የተለየ አሰራርና የንግድ ማዕቀፍ ተበጅቶለት በአንድ ቦታ የሚከወን የንግድ ሥርዓት ነው፡፡

ነጻ የንግድ ቀጠና ዓለም አቀፍ የንግድ ህጎች የሚደግፉትና ሌሎች አገራትም ተግባራዊ እያደረጉት የሚገኝ ነው። መንግሥት በሚፈልገው ቦታ ላይ በተለይም ከትራንስፖርትና ከሎጅስቲክስ እንዲሁም ከደረቅ ወደብ አገልግሎት ጋር ተያይዞ ቦታው የሚመረጥበት የራሱ



የነፃ ንግድ ቀጠናውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድ በከፈቱበት ወቅት

> **ነጻ የንግድ ቀጠናን አስመልክተው እንዳሉት፤ ነጻ የንግድ ቀጠና ማለት በአገሪቱ ያሉ ወይም ደግሞ ከዚህ ቀደም ሲሰራባቸው የነበሩ የንግድ ህጎች የማይመለከተው ሆኖ ለብቻው የተለየ አሰራርና የንግድ ማዕቀፍ ተበጅቶለት በአንድ ቦታ የሚከወን የንግድ ሥርዓት ነው**

መስፈርት አለው። ይህን መስፈርት መሰረት በማድረግም የራሱ አጥር ኖሮት የተከለለ ቦታ ይኖረዋል። በዛ ቦታ ላይ የሚስተናገደው ንግድ ማንኛውም በአገሪቱ ያሉ የንግድ ህጎች የማይገዙትና ቀለል ባለ ሁኔታ የሚስተናገድ የንግድ አሰራር ነው፡፡

ከሰሞኑም በድሬዳዋ ከተማ በሙከራ የተጀመረው ነጻ የንግድ ቀጠና ራሱን የቻለ የህግ ማዕቀፍ፤ ከአዋጅ ጀምሮ መመሪያና ፖሊሲ፤ እንዲሁም ራሱን የቻለና ቀጠናውን የሚቆጣጠር ተቆጣጣሪ ያለው ሆኖ የሚደራጅ ነው። ይህ በአንድ ቦታ የተከለለና የንግድ ሥርዓቱ ከተለመደው የንግድ ሥርዓት በተለየ መልኩ የሚከወነው ንግድ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ ነገር ግን የተለየ ዞን እንዳለ ተደርጎ የሚወሰድ የንግድ ቦታና ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ነው ብለዋል፡፡

በልዩ የኢኮኖሚ ዞን ውስጥ የተለያየ ነገር ማስቀመጥ ይቻላል የሚሉት አቶ እንዳለው፤ በአንድ አገር ውስጥ በተወሰነ ቦታ ተለይቶ የሚከወን ንግድ እንዳለ ሁሉ፤ መጠነኛ የሆኑ የማኑፋክቸሪንግ ሥራዎችም ይሠሩበታል ሲሉ ያብራራሉ። ለአብነትም መልሶ የማሸግና አሸጋው ከተከናወነ በኋላ የጽሁፍ መግለጫ ምርቱ ላይ ማድረግ፤ የጥራት ቁጥጥር ሥራና ሌሎችም ሥራዎች የሚከወኑበት ሲሆን በጥቅሉ አምራችነት፣ የንግድ ሥራ እና የሎጅተስቲክስ እንቅስቃሴ የሚደረግበት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሌሎች የንግድ ሥራዎች የሚከወንበት እንደሆነ ያብራሩት አቶ እንዳለው፤ በነጻ የንግድ ቀጠና ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የነጻ ንግድ ቀጠናው ተቆጣጣሪዎች፣ አስተዳደሮችና ከውጭም ሆነ በአገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች ይኖራሉ፤ ለእነዚህ አካላትም አግባብነት ያለው የሆቴል፣ የመዝናኛ እና የተለያዩ አገልግሎቶችን የሚሰጡ አካለትና ሌሎች የንግድ ሥርዓቶች በአካባቢው ይኖራሉ።

ነጻ የንግድ ቀጠናው የንግድ ነክ ህጎች ተፈጻሚ የማይሆንበት ቦታ እንደመሆኑ በእጅጉ ተመራጭ የሚያደርገው ነው ያሉት አቶ እንዳለው፤ የተለያዩ ማበረታቻዎችም የሚሰጡበት እንደሆነ ይገልጻሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ መንግሥት ይህን ነጻ የንግድ ቀጠና ተፈጻሚ ሲያደርግ ሁለት ነገሮችን ለማትረፍ ነው። አንደኛው አገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪና ተፎካካሪ እንዲሆኑ ለማድረግ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ የወጪና ገቢ ንግዱን እሴት በመጨመር ወጪ ቆጣቢና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ ነው። ስለዚህ መንግሥት በነጻ የንግድ ቀጠናው ምክንያት በወጪና በገቢ ንግዱ ከፍተኛ ተጠቃሚ መሆን ይችላል።

ቀደም ሲል በአገሪቱ የኢንዱስትሪዎች ፓርክ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን አቶ እንዳለው ይናገራሉ፤ ፓርኮቹ በአብዛኛው ወደ ሥራ የገቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ከሚገኙት ሼዶች ወደ ሥራ የገቡት ውስን መሆናቸውን ይገልጻሉ። ነጻ የንግድ ቀጠናው በዚህ ቦታ ሲጀመርም ብዙ ነጻ ሼዶች መኖራቸው አንዲሁም በዋናነት ደግሞ በአቅራቢያው የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጠት የሚችል ትልቅ መሰረተ ልማት በመኖሩ እንደሆነም ያብራራሉ።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ መንግሥት እዚህ ውሳኔ ላይ ሲደርስ የተለያዩ ገፊ ምክንያቶች በመኖራቸው ምክንያት ነው። አንደኛ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፤ ንግድን ለማስተዋወቅና ከፍተኛ ቁጥር ላላው የአካባቢው ማህበረሰብ የሥራ ዕድል መፍጠር ነው። ሌላው የወጪ ንግዱን በከፍተኛ መጠን ይጨምራል ተብሎ ይታሰባል። በተለይም በምርቶች የእሴት ሰንሰለት ላይ ትስስርን ያመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በእሴት ሰንሰለት ትስስሩም ጥሬ ዕቃውን የሚፈልግና በከፊል ያለቀለት ምርትን በማምጣት እዚሁ በአገር ውስጥ ተጠናቅቆ የሚሄድበት ሁኔታ ይኖራል። ይህም ከተለያዩ አገራት ጋር ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም የተለያዩ አይነት ምርቶችን በማምረት ኢኮኖሚ ውስጥ በአይነት ስብጥር ሊያመጣ የሚችል እንደሆነ አብራርተዋል።

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ መምህርና በ‹‹ፍሮንቲየርአይ (Frontieri)›› ጥናትና አማካሪ ድርጅት ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ሞላ አለማየሁ፤ ነጻ የንግድ ቀጠናን ምስራቅ አፍሪካን በአብነት ወስደው ያብራራሉ። ምስራቅ አፍሪካን እንደ አንድ በማየት ከምስራቅ አፍሪካ የሚገቡና የሚወጡ ወደ ምስራቅ አፍሪካ የሚወጡ ምርቶችን በአንድ ማስተሳሰር የሚችልና ለኢንፖርት ኤክስፖርት ንግዱ የተለየ አስተዳደር ያለውና የተቀላጠፈ የንግድ ሥርዓትን ማሳለጥ የሚችል እንደሆነ ያስረዳሉ።

እንደሳቸው ገለጻ፤ አንዳንድ ምርቶች ከቀረጥ፣ ከኮታና ከታሪፍ ነጻ የሆኑ ንግዶች አሉ። እነዚህን ዕድሎች ለመጠቀም ደግሞ ነጻ ንግድ ቀጠና ትስስር አስፈላጊ ነው። ከማን ጋር ምን አይነት የንግድ ስምምነት አለ የሚለው ተለይቶ ለተግባራዊነቱም የራሱ የሆነ ስትራቴጂ መንደፍ፣ ፕሮግራምና ቦታ በማዘጋጀት የሚከወን የንግድ አይነት ነው።

በኢትዮጵያ ለነጻ የንግድ ቀጠና ትስስሩ አሁን የተመረጠችው ድሬዳዋ ከተማ ምቹ እንደሆነች ዶክተር ሞላም ጠቅሰው፣ ድሬዳዋ አብዛኛው የአገሪቱ ወጪና ገቢ ንግድ የሚተላለፍባት ብቸኛዋ ቦታ ናት ይላሉ፤ በተለይም የወጪ ንግድ የሚካሄደው በድሬዳዋ ብቻ መሆኑን ገልጸው፣ ሁሉንም ንግድ በዚሁ ቦታ ላይ ማካሄድ መጨናነቅን ይፈጥራል። ኢኮኖሚው እየሰፋ ሲሄድ የሚፈጠረውን መጨናነቅ ለመቅረፍ ነጻ የንግድ ቀጠና ትስስርን መፍጠር ተገቢና ወሳኝ ነው ይላሉ።

ነጻ የንግድ ቀጠና ትስስር በአብዛኛው ጎረቤት ከሆኑ አገራት ጋር የሚደረግ የንግድ ስምምነት ነው የሚሉት ዶክተር ሞላ፤ ሌሎች አገራትን ሆኖ ማገልገል መቻልንም የሚጨምር እንደሆነ ነው የሚናገሩት፤ ለአብነትም ወደ ሶማሊያ የሚላክ ምርት ካለ፤ ልክ እንደ ሶማሊያ ሆኖ ማገልገል የሚያስችልና ሶማሊያ ላይ ባለው ነገር ኢትዮጵያ ላይ ማካሄድ፤ ኢትዮጵያ ላይ ባለው ነገር ደግሞ ሶማሊያና ኬኒያም ማካሄድ መቻል ማለት ነው። ባጠቃላይ በመሀል የሚፈጠሩ ክፍተቶችን በማስወገድ የተቀላጠፈ የንግድ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው ይላሉ፡፡

ነጻ የንግድ ቀጠና ከተለመደው የወጪ ገቢ ንግድ ምን የተለየ ነገር አለው ለሚለው ጥያቄ ዶክተር ሞላ ሲመልሱ፤ አሁን ላይ ያለው የወጪ ገቢ ንግድ ሁሉንም ያለ ልዩነት ማስተናገድ የሚችል እንደሆነ በመጥቀስ፣ ይህ ደግሞ ውጤታማነትን በከፍተኛ መጠን ይቀንሳል ነው የሚሉት። ነገር ግን ነጻ የንግድ ቀጠና ከማን ጋር ምን አይነት የንግድ ስምምነት አለን፤ እንዴትስ ነው የምናስተናግደው የሚለውን በትክክል ለይቶ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በፍጥነት የሚተገበርና ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ የሚያስችል ነው ብለዋል።

እንደ ዶክተር ሞላ ገለጻ፤ ማንኛውንም ወይም ደግሞ የቀረበውን ነገር ሁሉ ያለ ልዩነት ከማስተናገድ ይልቅ በተመረጡና በተወሰኑ ነገሮች ላይ መሰረት አድርጎ ማን ነው፤ ከየት መጣ፤ ምን አይነት ስምምነት አለን፤ የሚሉ ጥያቄዎችን መሰረት በማድረግ ከገቢ ኮታና ታክስ ጋር ምን ስምምነት አለ ብሎ ማስተናገድ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ የሚችል ነው። የተቀላጠፈ የንግድ እንቅስቃሴን ከመፍጠሩ በተጨማሪም ደንበኛን ለይቶ በአግባቡ ማስተናገድ የሚያስችል በመሆኑ የደንበኛን ቅሬታ በመፍታት እርካታን ይጨምራል፡፡

የድሬዳዋ ነጻ የንግድ ቀጠናን መርቀው የከፈቱት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ፤ ነጻ የንግድ ቀጠናው የሀገሪቱን የወጪና ገቢ ንግድ ለማሳለጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ብለዋል። ሌሎች ሀገሮች ነጻ የንግድ ቀጠና ከፍተው የእድገታቸው አጋዥ አርገው መጠቀም ከጀመሩ ብዙ አመታትን አስቆጥረዋል፤ እኛም ነጻ የንግድ ቀጠና መክፈታችን እድገታችንን ለማሳለጥ ያስችለናል ሲሉ አብራርተዋል።

የኢትዮጵያን ብልጽግና መሠረት እያጸኑ ለመሄድ መንቃት እና አዳዲስ አሰራር መጀመር አስፈላጊ መሆኑን በመግለጽ፤ ነፃ ቀጣናው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋ በመጣው አለም አቀፍ የንግድ ትስስር ኢትዮጵያ ተወዳዳሪ እንድትሆን የሚያስችላት መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ነፃ የንግድ ቀጣናው የአገሪቷን የወጪ እና ገቢ ንግድ ስርዓት የሚያዘምን ከመሆኑም በላይ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ስበት ከፍ የሚያደርግ መሆኑን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ ባለፉት አመታት በተለይ በግብርና ዘርፍ ትልቅ ውጤት መገኘቱን ገልጸዋል። የተገኘው ውጤት የበለጠ እንዲያድግ ነጻ የንግድ ቀጠናው ወሳኝ እንደሆነና ከድሬዳዋ በተጨማሪ በሌሎች የአገሪቱ የንግድ ኮሪደሮችም ነጻ የንግድ ቀጠናው አዋጭነት እየታየ እንደሚስፋፋ ነው ያመላከቱት።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፓሬሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሳንዶካን ደበበ ለነጻ ንግድ ቀጠናው የሚሆኑ መሰረተ ልማቶች የማሟላቱ ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉን ገልጸዋል፤ የሕግ እና የአሰራር ዝግጅት ስራዎች እየተጠናቀቁ መሆናቸውንም ጠቁመዋል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## አንዳንዴ ‹‹መቁረጥ›› ጥሩ ነው

ተገኝ ብሩ

ህይወት በተመሳሳይ ሂደት ውስጥ ስትሰነብት ትሰለቻለች። አንዳንዴ የተለየ ጣዕም መስጠት ይገባል። ለዚህ ደግሞ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እራስን ለየት ባለ ሁኔታ ላይ ማግኘት ጥሩ ነው። በሚገጥሙን አሉታዊ ነገሮች ደጋግመን የምንቆርጠው ተስፋ ይለመልም ዘንድ፤ ተበድረንም ቢሆን አንዳንዴ ቁርጥ መቁረጥ ጥሩ ነው። ወገን እውነቴ ነው ከሌላችሁ ተበድራችሁም ቢሆን ቁረጡ፡፡ሁሌ ተስፋ ብቻ መቁረጥ አይገባም።

ሰሞኑን "ዓለም ዘጠኝ ነው፤ አስር አይሞላ" የሚለውን መፈክር ተደግፌ፤ ምን አባቱ! የሚለውን ፉከራ ራሴን አስታጥቄ ለመቁረጥ ቆርጬ ተነሳሁ። ደጋግሜ የምቆርጠው ተስፋ እስኪ አንድ ቀን እራሱን ልቁረጠው ብዬ ወሰንኩ። ቁርጥ መቁረጥ አምሮኝ፤ መቁረጥ አሰኝቶኝ ልቆርጥ አሰብኩ። እንደ ሌላው ኢትዮጵያዊ የኑሮ መወደድ የደቆሰኝ ደሞዝተኛ ነኝና ውሳኔውን መወሰን ቀላል አልነበረም። ጊዜ ወስጄ መከርኩ፤ ከራሴ ጋር ብዙ ታገልኩ። ላድርገው፤ አላድርገው የሚል ሙግት ገጥሜ ለመቁረጥ ወሰንኩ። እና ወደ ቁርጥ ቤት ለመሄድ ተዘጋጀሁ፡፡

ወገን ‹‹ምግብ ብቻ ሲበሉት አይጥምም›› ይባል የለ! እውነት ነው። አብረውኝ የሚቆርጡ ወዳጆቼ ትውስ አሉኝ፤ ከሰው ጋር መቁረጥን አሰብኩ። ብቻዬን ከምሆን ብዬ በዚያውም ጨዋታውም ይደምቃል። በማቀርበው ተስፋ የተሞላበት ሀሳብ ደጋግመው ተስፋ የሚያስቆርጡኝ ጓደኞቼ ሀሳቤን ነገርኳቸውና ተስማሙ፤ እናም የመቁረጥ ምኞቴን ሙሉ አደረጉት። የደሞዝ ሰሞን ነበርና ከመካከላችን ብዙም ያንገራገረ አልነበረም። በወቅቱ የፆም መግቢያ ነበርና አጋጣሚውን ልንጠቀምበት ፈልገናል።

እየተጨዋወትን ስለ ቁርጥ እያወራን አራት ኪሎ አካባቢ ከሚገኙ ቁርጥ ቤቶች አንዱ ጋር ሳናስበው ደረስን። ከመካከላችን አንዱ ጓደኛችን ቤቱን በደንብ ያውቀው ነበርና "ኧረ ጎበዝ የዚህ ቤት ዋጋ ወገብ ይቆርጣል፤ ሌላ ቤት ይሻለናል" የሚል ሀሳብ ሲያነሳ በስንት ጊዜያችን ልንቆርጥ አስበን ክፈሉ በሚሉት ገንዘብ ወሽመጣችን ከሚቆረጥ ብለን እርምጃችንን ገታ አድርገን ተያየን። በነገራች ላይ አንድ አይነት ምግብ እያቀረቡ፣ ተመሳሳይ አገልግሎት እየሰጡ ዋጋቸው የምድርና ሰማይ ያህል የሚራራቀው ንግድ ቤቶቻችን ይገርሙኛል። ያለ ምክንያት ይቆልሉታል። የሚገርመው ደግሞ እዚያ እየተጋፉ የሚጠቀም ሰው መብዛቱ። እኛ ግን የመጋፋት አቅም የሌለን ነንና ቤቱን ትተነው ወደ ሌላ ለመሄድ ወሰን፡፡

እዚያው በአጋጣሚ በቆምንበት ምን ያህል እንደምናዋጣ ተነጋገርን። ልናዋጣ ያቀድነውና ልንገባበት ያሰብንበት ቤት ዋጋ የማይቀራረብ መሆኑ ግልፅ ነበር። ወይ የእኛ ነገር፤ በሆነ አጋጣሚ እንቁረጥ ብለንም ቅናሽ ፍለጋ መንገላታት። እንዲህ ነው ኑሮ፤ ይሄ ነው መልካችን።

ትንሽ በእግር ከተጓዝን በኋላ በዋጋው መካከለኛ ነው የተባለው ቤት ደጃፍ ደረስን። ቤቱ ከሩቅ ይጣራል። ዋጋቸው በአንፃራዊነት ጥሩ ነው፤ አገልግሎታቸውም መልካም የተባለበት ቤት ነው። ፆም መያዣ ነው አላልኳችሁም? ቤቱ ገበያ ሆኗል። ሰው ይተራመሳል። አዲስ አበቤ እዚህ ነው እንዴ የተሰበሰበው ያስብላል፡፡

የቤቱ መግቢያ ላይ ‹‹ከዚህ ቁረጥ ከዚያ ጨምር›› እያለ ቀዩን ከጮማ እየመረጠ የሚያስቆርጥ ተራ እስኪደርሰው በሰልፍ መልክ ተደርድሯል። ወደ ውስጥ ዘልቀን ስንገባ በዚያ በተንጣለለ ሰፊ አዳራሽ ውስጥ እያሽካኩ የሚቆርጡ፣ ጠረጴዛቸውን በመጠጥ ጠርሙሶች ሞልተው ከስጋ ጋር የሚታገሉ ሰዎች እዚያም እዚህም ተመለከትን።

ኑሮ ተወደደ የሚለው ሰው ተደብቆ እዚህ ሊቆርጥ ነው እንዴ የመጣው ያስብላል። ልብ አድርጉ እንግዲህ ቤቱ የፍየል ቁርጥ ብቻ የሚሸጥበት ቤት ነው። የበሬ ቁርጥ ቤትማ ስፍር ቁጥር የለውም።

> **ኑሮ ተወደደ የሚለው ሰው ተደብቆ እዚህ ሊቆርጥ ነው እንዴ የመጣው ያስብላል። ልብ አድርጉ እንግዲህ ቤቱ የፍየል ቁርጥ ብቻ የሚሸጥበት ቤት ነው። የበሬ ቁርጥ ቤትማ ስፍር ቁጥር የለውም**

አንዱ ጥግ ወንበር ስበን አረፍ አንዳልን እጅግ አጭር ቀሚስ የለበሰች ቆንጆ ወጣት ሴት ቀርባን "ምን ልታዘዝ" አለችን በትህትና። ያሻንን ታዘዝን። ቆርጠን አጥቅሰን አጣጥመንም በላን። በመጨረሻም ያ ክፉ ሰዓት ደረሰ። የክፍያ ሰዓት። ለአስተናጋጅዋ ሂሳብ ሰርታ እንድታቀርብልን ምልክት ሰጠናት፤ ይዛ ስትመጣ ሁላችንም ስንት እንደሆነ ለማየት ጓጓን፡፡

ታላቁ የህዳሴ ግድቡ ውሀ ሲሞላና ከላዩ ላይ ሲፈስ የነበረን ጉጉት አስታወሳችሁ? የሱን ያህል ነበር ስሜቱ። በእርግጥ ሁለቱ ጉጉቶች ይለያሉ። ያኛው የደስታ ጉጉት፤ ይሄኛው ደግሞ ስጋት የሞላበት፤ ምን ያህል ይሆን የመጣብን ጉድ የሚያስብል፡፡

ገለጥ አድርጌ አይቼው ፈገግ አልኩ። በደስታ አይደለም ፈገግታዬ በአግራሞት እንጂ። መካከለኛ ክፍያው ነው ለአገልግሎቱ የተባለው ቤት ጣራውን የነካ የሂሳብ ቁልል አቀረበልን። ጎኔ ላለው ጓደኛዬ አቀበልኩትና የሚደርስብንን ማስላት ቀጠልኩ። ሂሳቡ አንድ ኪሎ የፍየል ቁርጥ 1200 ብር ይላል። አራት ጎረምሶች ነን። ጠግበን በላን ነው ያልኩት ወገን። መቼም የበላነው አንድ ኪሎ አይሆን አይደል፡፡ የኪሎው ብዛት ገምቱና ሂሳቡን አስሉ። ክፍያው ጥሞን የበላነው ቁርጥ ለዛ አሳጣብን፡፡

ምነው ቀድመን በነገሩንና ቀስ እያልን እያጣጣምን በበላነው ያስብላል። ወይ ጉድ! እንዲህ ኪሳችንን እንገልብጥ። እንደምንም ኪሳችን ፈታትሸን ከፍለን ወጣን። በነገራችን ላይ ቁርጥ ቤቶች ኪሎ ታዘው ሙሉ ኪሎው አይደለም ለተጠቃሚ የሚያቀርቡት። ይህንን መታዘብ ችያለሁ። ስጠይቅ የእንጀራ እና የሚሰጠው አገልግሎት የሚካካሰው በዚያ መሆኑ በጥቆማ መልክ አንዷ አስተናጋጅ ነግራኛለች። ይሄም ህገወጥነት ነው። ቁርጥ ቤቶቹ ካልተጠየቁ በስተቀር ደረሰኝ ቆርጠውም ለተጠቃሚ አይሰጡም። አንድ ኪሎ 1200 ብር የሆነው፤ ፍየልዋን ስንት ቢገዙዋት ነው? ኧረ ተዉ ነጋዴዎች። ደግሞ የምትቀሻሽቡት ነገርስ አግባብ ነው? ስንቱን አላግባብ ሰብስባችሁ ትዘልቃላችሁ ጎበዝ? አንዳንዴ በምንቀርበው ቁርጥም ተስፋ ካስቆረጣችሁን ደንበኛ ከየት ልታገኙ ነው? በልክ አድርጉት እንጂ።

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ በዛፖሮዥ የኒውክሌር ጣቢያ ላይ ጥቃት ተፈጽሟል ስትል ከሰሰች

የሩሲያ መከላከያ ሚኒስትር ሰርጌ ሾይጉ በዛፖሮዥ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ደኅንነትን ጉዳይ ላይ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ጋር መክረዋል፡፡ሚኒስትሩ ከጉቴሬዝ ጋር በሥልክ በነበራቸው ውይይት ያነሱት ዩክሬን ጣቢያው ላይ ጥቃት መፈጸሟ ሩሲያ ላይ ትልቅ ሥጋት ፈጥሯል የሚል ነው፡፡

በኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ላይ በመድፍ እና በሰው አልባ አውሮፕላኖች የታገዘ ጥቃት ተፈጽሟል ስትልም ነው ሩሲያ በመከላከያ ሚኒስትሯ በኩል ስሞታ ያቀረበችው። ዩክሬን እና ምዕራባውያን ደጋፊዎቿ ደግሞ ሩሲያ ራሷ በምታስተዳድረው ቦታ ላይ ጥቃት እያደረሰች ዩክሬንን ትከሳለች በሚል ወቅሰዋል።

አሜሪካ እና የአውሮፓ ኅብረት በጉዳዩ ላይ ከዩክሬን ጎን የተሰለፉ ሲሆን የሩሲያ ወታደራዊ ኃይልም ቦታውን ለቆ እንዲወጣ ጠይቀዋል።አንቶኒዮ ጉቴሬዝ በበኩላቸው ÷ በጣቢያው አቅራቢያ ምንም ዓይነት ወታደራዊ ኃይል መኖር የለበትም ሲሉ አጽንኦት ሰጥተዋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞም በአካባቢው ነጻ ቀጣና እንዲቋቋም ጥሪ ማቅረባቸውን አር ቲ ዘግቧል።የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ማሪያ ዛካሮቫ ÷ የዩክሬን ታጣቂዎች ከኪየቭ በሚተላለፍላቸው ትዕዛዝ በኒውክሌር ጣቢያው ላይ ጥቃት እየፈጸሙ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ይሁን እንጅ የአውሮፓ ኅብረት ጥቃቱን ያደረሰችው ሩሲያ ናት የሚለው ዩክሬን በዓለም አቀፉ የአቶሚክ ኃይል ኤጀንሲ እንዳትከሰስ እና በፈጸመችው ጥቃትና ባደረሰችው ጉዳት እንዳትጠየቅ ነው ሲሉ የህብረቱን አቋም ኮንነዋል፡፡

የዛፖሮዥ የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ በደቡባዊ ዩክሬን የሚገኝ በአውሮፓ ትልቁ ለኤሌክትሪካ ኃይል ማመንጫነት የሚውል በሩሲያ የሚተዳደር ጣቢያ መሆኑን መረጃዎች እንደሚያመለክቱ ኤፍቢሲ ዘግቧል፡፡

## ዩናይትድ ኪንግደም ለታዳጊ ሃገራት ምርቶች የቀረጥ ቅነሳ ልታደርግ ነው



ዩናይትድ ኪንግደም የንግድ ግንኙነቷን ለማሳደግ ከታዳጊ ሃገራት ከምታስገባቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ምርቶች ላይ ቀረጥ ልትቀንስ ነው።የታዳጊ ሃገራት የንግድ ዕቅድ በጥር ወር ተግባራዊ ይሆናል። ይህም እንግሊዝ የአውሮፓ ህብረት አባል በነበረችበት ጊዜ በነበረው ዕቅድ ላይ ይመሠረታል ተብሏል።

በእንግሊዝ ውስጥ በስፋት የማይመረቱ እንደ ልብስ፣ ጫማ እና ምግቦች ያሉ ዕቃዎች ዝቅተኛ ወይም ዜሮ ታሪፍ ይጣልባቸዋል። ዕቅዱ 65 ታዳጊ ሃገራትን ያጠቃልላል ተብሏል።ዕቅዱ በማደግ ላይ ያሉ ሃገራት ያለ ታሪፍ ወደ እንግሊዝ የሚልኳቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ምርቶችን አያካትትም። በተጨማሪም 99 በመቶ ከአፍሪካ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

የዓለም አቀፍ ንግድ ቢሮ እንደገለጸው ዕቅዱ ንግድን "ዕድገት ለማስመዝገብ እና ድህነትን ለማጥፋት" እንዲሁም የእርዳታ ጥገኝነትን ለመቀነስ እንግሊዝ የምታደርገው ጥረት አካል ነው።ዕቅዱ ሃገራት በሰብዓዊ መብት፣ በጉልበት ብዝበዛ ወይም በአየር ንብረት ለውጥ ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት የማገድ ስልጣንን ያካትታል።

የዓለም አቀፍ ንግድ ኃላፊ የሆኑት አን-ማሪ ትሬቬሊያን እንዳሉት "የንግድ ፖሊሲያችንን እንደገና እየተቆጣጠርን የዩናይትድ ኪንግደም ንግዶችን የሚደግፉ ውሳኔዎችን ከመውሰድ ባለፈ በኑሮ ውድነት እና የታዳጊ ሃገራትን ኢኮኖሚ ይደግፋል።"

ከ65 ድሃ ሃገራት ከጨርቃጨርቅ እስከ ፍራፍሬ የሚደርሱ ምርቶች በዩናይትድ ኪንግደም ሲሸጡ የአነስተኛ ወይም የዜሮ ታሪፍ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ይህም ይበልጥ ተፎካካሪ ያደርጋቸዋል።አዲሱ ዕቅድ የተወሰኑትን ተጨማሪ ክፍያዎችም ይቀንሳል ተብሎ ይጠበቃል።

ለውጦቹ አስመጪዎችን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ፓውንድ እንዲያድኑ ያግዛሉ። ሆኖም ሙሉ በሙሉ ቢተገበር እንኳን ለተጠቃሚዎች የሚደርሰው የዋጋ ቅናሽ አነስተኛ ሊሆን ይችላል።ለታዳጊ አገሮች የሚሰጠው ዕርዳታ በመቀነሱ በምትኩ መንግሥት በንግድ የመደገፍ ፖሊሲ እንዳለው ያሳያል ተብሏል።

ከወቅቶች መለዋወጥ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ምርቶች እንግሊዝ ውስጥ መመረት በማይችሉበት ወቅት በምርቶቹ ላይ የሚጣለው አነስተኛ ታሪፍም ይነሳል።አንዳንድ ደንቦችም ቀላል ይሆናሉ። ለምሳሌ አንድ ምርት አብዛኛውን ግብዓቶቹን ከየት ነው የሚያገኘው በሚል የምርቱን ሃገር የመወሰን ጉዳይ አንዱ ነው።

በጨርቃጨርቅ ዘርፍ የተሰማራው የባንግላዲሹ የዲቢኤል ግሩፕ ሥራ አስኪያጅ መሐመድ ጃባር ዕቅዱ ለድርጅታቸው "ትልቅ ለውጥ" መሆኑን ቀይረዋል።"በለውጦቹ ምክንያት ጥጥ ቀድም ሲል ከምናገኝባቸው ሃገራት በተጨማሪ ከሌሎችም በርካታ ሀገራት ማግኘት እንችላለን ማለት ነው። ይህም ንግዱን የበለጠ ተወዳዳሪ እና የአቅርቦት ሰንሰለቶቻችንን በጣም ጠንካራ ያደርገዋል" ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

## ተሰማ ሀብተሚካኤል (1882 – 1952)

ግርማ መንግሥቱ

ከዚህ በፊት፣ ምናልባትም ከሁለት ወራት በማይበልጥ ጊዜ፣ ከዛሬው እንግዳችን ጋር በተመሳሳይ ተግባር የሚታወቁ ሁለት አንጋፋና የአገር ባለ ውለታ ምሁራንን አስታውሰን፤ ባለውለታነታቸውንም ዘክረን ነበር።

‹‹'አስተማሪዬ መምህር ክፍለ ጊዮርጊስ የጀመሩትን ግዕዝ አማርኛ ግስ እንድጨርስ አዘውኝ ነበር። እነሆ እስከ ዛሬ ደክሜበታለሁ፤ አልተጠናቀቀልኝምና አንተ ተረክበኸኝ ሥራውን ቀጥል። ዘርሁን፤ ዘር ይውጣልህ' ብለው አለቃ ኪዳነ ወልድ ለአለቃ ደስታ አደራ ሰጥተው ነበር። አለቃም አደራውን ጠብቀው በ1948 ዓ.ም. ከመደበኛ ሥራቸው ውጭ ሌት ከቀን በመሥራት ‹‹መጽሐፍ ሰዋሰው ወግስ፤ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ›› የተባለውን የመጀመሪያ ታላቅ መዝገበ ቃላት አሳትመዋል፡ ፡" የሚለውን ሀሳብም (የትውልድ ቅብብሎሽን በሚያሳይ መልኩ) ምንጭ ጠቅሰን አስፍረናል።

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌን በተጨማሪ "አለቃ ደስታ ተክለ ወልድ (ሐምሌ 19 ቀን 1893 ዓ.ም – ጳጉሜን 2 ቀን 1977 ዓ.ም)" በሚል ርእስም ስለ አለቃ ደስታ ገፃችን የፈቀደልንን ያህል ብለናል። የዛሬውም የዛው "ፓኬጅ" ተደርጎ ይወሰድልን ዘንድ እየጠየቅን ባለውለታችንን፣ በስማቸው "ከሳቴ ብርሃን ሰንበት ትምህርት ቤት" (ወደ ፊት አንድ ዩኒቨርሲቲ በስማቸው መሰየሙ መቸም አይቀርም) የተሰየመላቸውን ታላቅ ሰው ወደ መዘከሩ ተግባር እንሸጋገራለን።

ስለ አማርኛ መዝገበ ቃላት ሲነሳ የዛሬ 60 እና 70 ዓመት የአሜሪካ መንግስት ያዘጋጀው አማርኛን በድምጽ የሚያስተምርና የሚተረጉም መሳሪያና በ1841 ዓ.ም በዊልያም ኢዘንበርግ የተጻፈው "የአማርኛ መዝገበቃላት" ፤ እንዲሁም በ1690 ዓም የታተመው የአማርኛ እና ላቲን መዝገበ ቃላት ወደ አእምሯችን መምጣታቸው አይቀርም። A Dictionary of the English Language፤ በሌላ ስሙ Johnson's Dictionary (1775)ም እንዲሁ።

በ1859 ዓ.ም በቤንጋል፣ ህንድ የታተመው የአማርኛ–ኡርዱና–እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላትም ሆነ በ1833 ዓ.ም በቄስ ቻርለስ ዊሊየም ኢዘንበርግ እንግሊዝ (ለንደን) የታተመው የአማርኛና እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት እንደ አንድ ቀዳሚ ስራ ሳይታወሱ የሚታለፉ አይደሉም።ይህ መዝገበ ቃላት በመጀመሪያ ክፍሉ አማርኛን ወደ እንግሊዝኛ የሚተረጉም ሲሆን፤ በሁለተኛ ክፍሉ መልሶ እንግሊዝኛን ወደ አማርኛ የሚተረጉም መሆኑን መረጃዎች ያመለክታሉ።

(ቻርለስ ኢዘንበርግ (እ.ኤ.አ. መስከረም 5 ቀን 1806 ስቱትጋርት -- ጥቅምት 10 ቀን 1864) የአንግሊካን ቤተክርስቲያን ቄስ የነበረና ባለፈው ዘመኑ የቆርቆሮ ብረት አንጥረኛ የነበር ሰው ነው። ቄስ በነበረበት ዘመኑ ወደ ኢትዮጵያ እና ህንድ የተላከ ሚሲዮናዊ ሲሆን ይሄውም (እ.ኤ.አ) ከ1832-1864 መሆኑ ነው። ኢዘንበርግ፣ ከ'34-38 በአድዋ ትግራይ የኖረ ሲሆን ከአካባቢው ቀሳውስት ጋር መግባባት ስላላሰየ ሊባረር በቅቷል። በሚቀጥለው አመት፣ 1839፣ በሸዋው ንጉስ ሣህለ ሥላሴ ግብዣ እርሱና ሌሎች ሁለት ሚስዮኖች ሸዋ ሄዱ። ከ4 ወር ቆይታ በኋላ ኢዘንበርግ ወደ ለንደን እንግሊዝ ተመልሶ ሄደ። በለንደን ቆይታው ብዙ መጻህፍትን በአማርኛ ና ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አሳትሟል። እነርሱም አፋርኛ፣ኦሮምኛ (ከሉድቪግ ክራፍ የተወሰደ) እና አማርኛ መዝገበ ቃላት (1840-42)፣ የአማርኛ ሰዋሰው፣ የቤተክርስቲያን ታሪክ፣ ጂኦግራፊ፣ እና የዓለም ታሪክን ያቅፋሉ። ኢዘንበርግ በ1842 እንደገና ወደ ሸዋ ለመመለስ ሞክሮ ነበር፤ ሆኖም ግን ፍቃድ ስለተከለከለ ወደ ትግራይ በማምራት በዚያ እስከ 1843 ተቀመጠ። ደጃዝማች ውቤ በዚሁ አመት ከትግራይ ስለአባረሩት ወደ ለንደን አመራ። በ1844 የአቡ ሩሚን የቆየ አማርኛ መጽሓፍ ቅዱስ ትርጓሜ በማረም ከክራፕፍ ጋር አሳተሙ። በዚያው አመት አራቱን ወንጌሎች በትግርኛ ቋንቋ ሊያሳትም በቃ። ይህ የትግርኛ መጽሀፍ ቅዱስ በበርሊን፣ ጀርመን ይገኛል። የሚለውን ከድረ-ገፅ የተገኘ መረጃ እዚህ ጋ በቅንፍ አስቀምጠነዋል ።)

ከዘመናዊነት (የቅርብ ህትመት ከመሆኑ) አኳያ፣ 90 አመታትን የፈጀውና (በ1921 የጀምሮ በ2011 የተጠናቀቀው) በ26 ጥራዞች የተዘጋጀው፤ ከ2500 ዓ.ዓ ጀምሮ እስከ 100 ዓ.ም በሶርያ፣ በቱርክ፣ በኢራቅና በኢራን ይነገሩ የነበሩትን ቋንቋዎችና ቀበሌኛዎች ያካተተው፤ በዩናይትድ ስቴትስ የሚገኘው የቺካጎ ዩኒቨርሲቲ የምሥራቃዊ አገሮች ጥናት ተቋም ያዘጋጀውና በዘርፉ ባለሙያዎች ዘንድ ትኩስ ዜናነቱ ቀዝቀዝ ያላለው ከ9ሺህ 700 የሚበልጡ ገጾች ያሉት "የአሥር ቋንቋ መዝገበ ቃላት" (The Assyrian Dictionary) .... እና ሌሎች በርካታ ስራዎች ይታወሱን ይሆናል።

ከመለስተኛ 2ኛ ደረጃ እስከ 2ኛ ደረጃ የዘለቀ፣ አምሳሉ አክሊሉ ከፈረንጁ ጓደኛቸው ጋር ያዘጋጁትን "አማርኛ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት" ማን ይረሳል? አቅም ያለውና ህይወቱ ከምርምር ስራዎች ጋር የተቆራኘ ዌብስተርና ኦክስፎርድን ከጠረጴዛው ላይ እንደማያጣው ሁሉ፤ ባለፈውም ሆነ ዛሬ እዚህ የምናስታውሳቸው ባለውለታዎቻችን (አለቃ ኪዳነ ወልድ፣ አለቃ ታዬ እና የዛሬው ከሳቴ ብርሀን) ስራዎችም እንዲሁ ከጠረጴ ላይ የሚጠፉ አይደሉም። ይላቅ ኃይለማርያም ያሳተሙት ሐበሻ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1995)ም አለ። የደራሲ ባህሩ ዘርጋውም እንዲሁ ይጠቀሳል። በተለይ ሊታይ ይገባል ካልተባለ በስተቀር የሥርግው ሐብለሥላሴ (ዶ/ር) "የአማርኛ የቤተክርስቲያን መዝገበ ቃላት"ም ተጠቃሽ ነው።

ሁሉም ይጠቀሱ እንጂ የቀደምቶቹን ያህል የተፈላጊነትን ስፍራ የተቆጣጠረ አለ ለማለት የሚያስደፍር አንዳች ምክንያትም ሆነ ማስረጃ የለም።

በ"የአማርኛ መዝገበ ቃላት" (ከሳቴ ብርሃን ተሰማ፣ 1951 ዓ.ም፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ) እውቅና ዘመን ተሻጋሪ (ብዙዎች አውደ ጥበብ (ኢንሳይክሎፔዲያ ነው ይሉታል - ከመዝገበ ቃላት በላይ መሆኑን ለመግለፅ)) ስራቸው ከፍ ብለው የሚታወቁት ተሰማ ሀይለሚካኤል በደራሲያን ማህበር የአንድ ወቅት አጀንዳ ላይ የሚከተለው ሰፍሮላቸው ለንባብ በቅቷል፤

ተሰማ ሀብተሚካኤል በሰሜን ሸዋ በሰላሌ አውራጃ ጎሐጽዮን በ፲፰፻፹፪ (1882) ዓ.ም. ተወለዱ። ተሰማ የዓባይን ወንዝ አቋርጠው ወደ ጎጃም በመሄድ ዜማ፣ ትርጉም (ትርጓሜ፣ ቅኔን ... በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተከታትለዋል። በተለይ ዲማ ወደ'ሚገኘው እውቅ ገዳም በመሄድ ዜማና ቅኔ ተምረዋል። የቤተክርስቲያን ከፍተኛ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ በኋላ በ፲፱፻፩ (1901) ዓ.ም. በመንግሥት ሥራ በመቀጠር ወደ ሐረርጌ ጠ/ግዛት ሄዱ። ተሰማ በጥሩ እጅ ጽሑፋቸውና በተለየ የፊደል አጣጣላቸው ይታወቁ ነበር። ብዙ የሃይማኖት መጻሕፍት እንዲገለብጡ ይታዘዙ የነበረውም ለዚህ ነው። በጡረታ እስከተገለሉበት ፲፱፻፶፬ (1954) ዓ.ም. ድረስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት እንዲያዘጋጁ በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ኃላፊነት ተሰጧቸው ሠርተዋል። "ከሣቴ ብርሃን" የተሰኘው ሥራቸው ጠንካራ፣ ዋነኛና ትልቁ ሥራቸው ነው።

በማህበሩ አጀንዳ ላይ እንደ ተገለፀው፣ በዚህ መዝገበ ቃላት ዝግጅት ላይ እንደነበሩ ብዙ ችግሮችና መሰናክሎች ገጥመዋቸዋል። አማርኛ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሲሆን፤ እንግሊዝኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ አደሪኛ እና ግዕዝ ጠንቅቀው ያውቃሉ። ይህን የቋንቋ ዕውቀታቸውንም በተለያዩ ሥራዎቻቸው ላይ በሚገባ አውለውታል። ጥንካሬያቸውም "ከሳቴ ብርሃን" በተባለው መዝገበ ቃላት ዝግጅት ላይ ተገልጧል፡፡

ከአሥር ዓመታት በኋላ ባለ 1ሺህ 398 ገጾች መዝገበ ቃላት ሲያዘጋጁ፣ መዝገበ ቃላቱም 33ሺህ ድርሰቶች፣ አገባቦች እና 1ሺህ 278 ሥዕሎች ሲኖሩት ከተጀመረ 12 ዓመታት በኋላ በገበያ ላይ ለመዋል ችሏል። ስሙም ለደራሲው ክብር ሲባል "ከሣቴ ብርሃን ተሰማ" እንዲባል በትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር ተመርጦ ተሰየመ። ይህም ለተሰማ ሀብተሚካኤል እንደ ሽልማት ተቆጠረ፡፡

እኚህ ብዙም ያልተነገረላቸው፣ ያልተፃፈላቸው ... ባለውለታ ታሪካቸው ወደ ፊት ተበጥሮ ይወጣል የሚል እምነት ያለን ሲሆን፤ ለአሁኑ ማለት የምንችለው ከማንም በላይ የለፉ ሆነው፤ ከማንም በላይ የተጉ ሆነው ... ሳለ ብዙም ሲነገርላቸው አለመሰማቱ ተገቢ አይደለም የሚል ትዝብት የለንም ማለት ግን አይደለም።

ዛሬ "መዝገበ ቃላት" የሚለውን አስቀድመው ወይም አስከትለው (እንደየ ቋንቋው ማለት ነው) አደባባይ የወጡ መዝገበ ቃላት በርካቶች ናቸው። በእውነት ደስ ይላል።

እርግጥ ነው አንድ መዝገበ ቃላት በዋናነት ቢያንስ አምስት ጉዳዮችን ማስተናገድ (ጥያቄዎችን መመለስ) አለበት የሚል ሙያዊ ድምዳሜ አለ። ወይም እራሱ የመዝገበ ቃላት አዘገጃጀቱና አላማው እነዚህን ዋና ዋና ጉዳዮች በመሰረታዊነት ሊይዝ ይገባል።

እነዚህ ዋና ዋና ጉዳዮች (ወይም፣ ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች) ንበት (ፐሮናውንሴሽን)፣ ብያኔ (ዴፊኒሽን)፣ ትርጉም (ሚኒንግ)፣ ቃሉ መቼ እንደተፈጠረ፣ የቃሉን የንግግር ክፍል (ስም፣ ግስ...)፣ የት እንደተፈጠረ ... መመለስ ሲሆን፤ "ዛሬ በተለያዩ የአገራችን ቋንቋዎች እየተዘጋጁ ያሉት ምን ያህል እነዚህን መሰረታዊ ጉዳዮች አስተናግደዋል?" የሚለውን እዚህ መነጋገር ባይቻልም፤ በዛን ዘመን የተዘጋጀው የተሰማ ሀይለሚካኤል "ከሳቴ ብርሀን የአማርኛ መዝገበ ቃላት" (የመጽሐፉ የ2008 እትም ዛሬም mereb.shop ላይ 36.05 ዶላር እየተቸበቸበ ይገኛል፤ ይህም ውድ ዋጋ መሆኑን ልብ ይሏል።) ግን በዚህ እንደማይታማ ተደጋግሞ የታየ፤ የተመረመረ፤ ተመርምሮን ይሁንታን ያገኘ ጉዳይ ነው።

መቼም ጥናትና ምርምርንም ይሁን ማንኛውንም አይነት በሳል ጽሑፍ የሚያዘጋጅ ሰው የከሳቴ ብርሃን ተሰማን "የአማርኛ መዝገበ ቃላት"፤ የኪዳነ ወልድ ክፍሌን "መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ"ንና ሌሎችንም ሳይጠቅስ፤ ወይም፣ ከእነዚህ መካከል አንዱን ዋቢ ሳያደርግ ይቀራል ማለት ዘበት ነው። በተለይ ለቃላት ብያኔን መስጠት የግድ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ እነዚህን ቱባ ቱባ ራዎች ማገላበጥ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው። ይህንን በምሳሌ እንየው ካልን በአንድ መጣጥፍ ውስጥ ያለውን፤ ስለ "ኑፋቄ" ምንነት የሚያብራራውና፤

እንደሚሰጡት ፍቺ ከሆነ፣ "ኑፋቄ" "ነፈቀ – ከሃይማኖት ወጣ፣ ተጠራጠረ፣ መናፈቅን፣ ከሓዲን ኾነ ነፈቀ፡፡" የሚል ትርጉም ይይዛል። በዚህ ትርጉም መሠረት "ነፈቀ" ማለት ከትክክለኛው የእምነት መንገድ ወጣ፣ ሳተ ወይም ትክክለኛውን እምነት ካደ፣ ተጠራጠረ ማለት ነው። የኪዳነ ወልድ ክፍሌም፤ "መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ" ደግሞ "መናፍቅ (ቃት፣ ቃን) ናፈቂ፣ አናፈቂ፣ የሚጠራጠር፣ የሚያጠራጥር፣ ጠርጣሪ፤ ሃይማኖቱ ሕጹጽ የሆነ፣ ሙሉ እና ፍፁም ትክክል ያይደለ፤ መንፈቁን አምኖ መንፈቁን የሚክድ፡፡ " አለቃ ኪዳን ወልድ ክፍሌ በበኩላቸው መናፈቅ ማለት እምነቱ ትክክል ያልሆነ፣ ግማሽ እውነት ግማሽ ሐሰት የሆነ እምነት ማለት ነው የሚለውን ያክላሉ፡፡

የሚለውን። እንዲሁም፣ "በገና" የሙዚቃ መሳሪያ (መንፈሳዊ)ን በተመለከተ ከቀረበ ጽሑፍ ያገኘነውን እንመልከት፤

አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ "መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ" በሚል መጽሐፋቸው በሁለት መልኩ ማለት "ሲጠብቅና ሲላላ" ብለው በማመሳጠር እንዲህ ብለው ተርጉመውታል። በገና፡- በዕብራይስጥ ናጌን ይባላል ካሉ በኋላ ሲተረጉሙት፡- ነዘረ፣ መታ፣ ደረደረ፣ ማለት ነው። ሲጠብቅ ግን፡- ነደደ፣ ተቆጣ... ያሰኛል ብሏል፡፡

በገና፡- በቁሙ መዝሙር ማለት ነው ብለውም ፈትተውታል። (አለቃ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ፡ መጽሐፈ ስዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ) አባ ዮሐንስ ገ/እግዚአብሔር የትግርኛ መዝገበ ቃላት በተባለ መጽሐፋቸው፡- በገናን በቁሙ በገና ብለው ተርጉመውታል። (አባ ዮሐንስ ገ/እግዚአብሔር፣ ትግርኛ አማርኛ መዝገበ ቃላት፣ 1948፣ አሥመራ) ከሳቴ ብርሃን ተሰማ "የአማርኛ መዝገበ ቃላት" በተሰኘ መጽሐፋቸው እንዲህ ዓይነት ትርጉም ሰጥተውታል፡፡

– በገና፡- በአሥር አዉታር ጅማት በገናን ሠራ፣ ቃኘ፣ ደረደረ፣ ድምጽን እያጣራ፣ እያጣቀሰ፣ እየነዘረ... በገናን በገነ... ካሉ በኋላ – በገነኛ፡- የሚለው ደግሞ በገናን የሚመታ፣ በገናን የሚያውቅ ደርዳሪ... ማለት ነው ብለው ተርጉመውታል፡፡

ከዚህ የምንገነዘበው የመዝገበ ቃላት ፋይዳ ከዚህ በመላስ የማይባል ብቻ ሳይሆን፤ ፋይዳው የማይተካና የማይታለፍም መሆኑን ነውና ባለፈው ያስታወስናቸው ባለውለታዎቻችንም ሆኑ የዛሬው (ከሳቴ ብርሃን ተሰማ) ተሰማ ሀብተሚካኤል (ልክ የእንግሊዝኛ ዲክሽነሪ ሲነሳ Father of the Modern Dictionary በሚል ማህበራዊ ማእረግ ስሙ የሚታወቀው ሳሙኤል ጆንሰን ሳይነሳ እንደማይታለፈው ሁሉ) "ሰው ያደረጉን" ናቸውና ሌሎችም አርአያነታቸውን ሊከተሉ እንደሚገባ ይሰማናል። በሌላው አለም ለእነሱ አይነት ሰዎች የሚሰጠው ማህበራዊ ስፍራ ወደዚህም መጥቶ እነሱም ተገቢ ውለታቸው ይከፈላቸዋል፤ በመጪው ትውልድም ሲዘከር ይኖራል ብለን እናምናለን።



The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ረቡዕ
አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የፌዴሬሽኑ ጠቅላላ ጉባኤና ምርጫ በተያዘለት ቀን ይካሄዳል

**ቦጋለ አበበ**

ከአስር ቀናት በኋላ በጎንደር ከተማ የሚካሄደው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤ ፌዴሬሽኑን ለቀጣይ አራት አመታት የሚመሩ የፕሬዚዳንትና የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ምርጫ በታቀደው ቀን እንደሚካሄድ ተገለጸ።

የምርጫ አስፈጻሚና የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴዎች ከትናንት በስቲያ በጋራ በሰጡት መግለጫ እስካሁን ያከናወኑትን ስራ በዝርዝር ያቀረቡ ሲሆን ምርጫውም በታቀደው መሰረት እንደሚከናወን አስረድተዋል። ግንቦት 7/2014 ተመርጦ ባለፉት 55 ቀናት የተለያዩ ስራዎቹን እየሰራ የነበረው የአስመራጭ ኮሚቴው " 3 ለፕሬዚዳንትነትና 26 ለስራ አስፈጻሚነት ዕጩ ሆነው የቀረቡትን ግለሰቦች ቀደም ሲል ይፋ ማድረጉን አስታውሶ፣ የዕጩዎችን ዝርዝር ከተቻለ ከነሀሴ 12 በፊት ካልተቻለ ደግሞ በነሀሴ 22 ምርጫው በሚከናወንበት ዕለት ለጉባኤተኞች ይፋ እንደሚያደርግ ጠቁሟል። የቀረው ነገር የጉባኤው መካሄድ ብቻ እንደሆነም የኮሚቴው በሰብሳቢ በአቶ ሀይሉ ሞላ አስረድቷል።

በቀረበው የተገቢነት ጥያቄ ዙሪያም " ከጉባኤተኛውም ሆነ ከፊፋ የቀረበ ተቃውሞም ይሁን ቅሬታ የለም ሼር ካምፓኒው የጉባኤው አባል ባለመሆኑ የምንለው ነገር የለም በእኛ በኩል የፌዴሬሽን አካላት ናቸው መሳተፍ አይችሉም ብሎ ካፍ በዝርዝር የከለከለው የኦዲት ኮሚቴ ፣ የስነምግባር ኮሚቴ፣ የዲሲፕሊን ኮሚቴና የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን ነው ከዚያ ውጪ ማንንም አይከለክልም" ያሉት አቶ ሃይሉ "የዛሬ አራት አመት ምርጫ ኮሚቴና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ መሃል ጸብ ተነስቶ መሰነጣጠቅ በመኖሩ ምክንያት ፊፋና ካፍ መጥተው ሁለቱን ወገኖች አሰናብተው ሌላ አስመራጭ ኮሚቴ



ሁለቱ ኮሚቴዎች ምርጫውን በተያዘለት ቀን ለማካሄድ እንቅፋት የሚሆን ችግር እንዳልገጠማቸው ገልጸዋል፣

ተመርጧል አሁንም እንዳለፈው አራት አመት ለመሰነጣጠቅና ለማጣላት ተሞክሮ ከሽፏል አሁንም አይደገምም አይሳካም" ሲሉ ተናግረዋል።

"ካፍና ፊፋ ሊመጡ ነው ብለን አንሰጋም ከመጡና ልክ አይደሉም ከተባለ ይቆማል ነገር ግን የሚያስቆም ነገር ሰርተናል ብለን አናምንም ያሉት የኮሚቴው ጸሀፊ አቶ መንግስቱ መሃሩ "በኢትዮጵያ እግርኳስ ፌዴሬሽን ደንብና ተሻሽሎ የቀረበ አዲስ የምርጫ ደንብ መሠረት የቀረቡ ዕጩዎች ህጋዊ ናቸው የሚለውን አይተን የመጨረሻውን ወስነናል የተነሳው የተገቢነት ጥያቄ ግን አያሳስበንም" ሲሉ ያለውን ሂደት አስረድተዋል።

በሂደቱ ዙሪያ የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በአቶ ብርሃኑ ከበደ አማካይነት በሰጠው ምላሽ " የህግ ሰው በሌለበት ሰዓት አንሰራም ልቀቁን ስንል ባላችሁበት ቀጥሉ ብለውን ሰርተናል በኮሚቴው ውስጥ የህግ ሰው ይኑር ይላል ነገር ግን የተቀመጠ ከልካይ ህግ ባለመኖሩ ስራውን ሰርተናል አጠቃላይ ሂደቱን ለጠቅላላ ጉባኤው የምናሳውቅ ይሆናል " ሲሉ መልሰዋል።

ለፕሬዚዳንትነት ከቀረቡ ዕጩዎች መካከል አንዱ በነበሩት አቶ ገዛኸኝ ወልዴ የምርጫ ክልከላ ዙሪያ ኮሚቴው በተሰጠው ምላሽ "አቶ ገዛኸኝ የሉበትም ብሎ ምርጫ ኮሚቴ ያስቀረውን ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ተቀብሎ ማየት አልቻልም ደንቡም ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የሚያየው አስመራጭ ኮሚቴ የወሰነውን ጉዳይ ብቻ ነው ስለሚል የአቶ ገዛኸኝ ይግባኝን ለማየት አልቻልንም፣ በተገቢነት ጉዳይ የተነሳው ጥያቄ ግን የኮሚቴውን አባላት አይመለከትንም" በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

በአቶ ገዛኸኝ ዙሪያ አስመራጭ ኮሚቴው በሰጠው ምላሽ "የሀረሪ ክልል የወከለውን ውክልና አንስቻለሁ ብሎ ደብዳቤ ላከ በህጉ መሠረት ተቀባይነት ያለው ጥያቄ በመሆኑ ውክልናው ተነሳ። እንደ ኮሚቴው በቀጥታ የተነጋገርነው ከክልሉ እንጂ ከአቶ ገዛኸኝ ጋር አይደለም ክልሉ በግልባጭ ለላከላቸው ሁሉ ውሳኔያችንን በግልባጭ አሳውቀናል፣ ኮሚቴው የዘጋውን ጉዳይ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ያላየውም ለዚህ ነው" ሲል ሂደቱን አስረድቷል።

ሁለቱም ኮሚቴዎች የተጣመራችሁ መሆኑ ፍትህ አያዛባም ወይ ለአንድ ወገን የማድላት ሂደትንስ አይፈጥርም ወይ? ለተባለው ጥያቄ የአስመራጭ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሀይሉ በሰጡት ምላሽ "ሁለቱም ኮሚቴዎች ተያያዥነት የላቸውም ግልጽነቱን ለማስፈን ብለን ነው አብረን የቀረብነው፣ ውስጣችን ምንም አይነት ሽፍጥ የለም ተለያይታችሁ መቅረብ ነበረባችሁ ካላችሁ ለወደፊቱ እንማራለን" ሲሉ ተናግረዋል።

"ፍቅር አያስፈራም መጣላት ነው የሚፈራው የይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔን እንኳን የሰማነው ከመግለጫው 5 ደቂቃ በፊት ነው" ያሉት አቶ መንግስቱ "የፌዴሬሽኑ ደንብን ተመልከቱ በጣም መሻሻል ያለባቸው ህጎች አሉ የሀገር እግርኳስ የሚያሳድጉ ሰዎች ወደ ፌዴሬሽኑ የሚመጡበት መንገድ ጠንክረን መስራት አለብን" ሲሉ ተናግረዋል።

ፊፋ ከ6 ወር በፊት አሳውቁ እያለ እናንተ በ4 ወር ውስጥ ማሳወቃችሁ ፊፋ ሊቀጣን አይችልም ወይ ? የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አቶ ሃይሉ "ፊፋ ከ6 ወር በፊት የሚል ህግ ባለበት በ4 ወር ውስጥ ሲካሄድም ያውቃል፣ ከጠቅላላ ጉባኤ ምርጫ አንስቶ እያንዳንዱን ጉዳይ ያውቃል ጸጉር ስንጠቃ አያስፈልግም፣ እናም መቼ ይካሄድ መቼ ይጨረስ የሚለውን ሁሉ ፊፋ ያውቃል፣ በዚህ አንሰጋም እስካሁኗ ደቂቃ ድረስ ስጋት የለብንም ፊፋ ጥቃቅን ነገር እየሰነጠቀ የሚሄድ ተቋም አይደለም፣ ህግ እንዳለ አይተረጎምም የሚታዩ ጉዳዮች ከግምት የሚገቡ ነገሮችም አሉ" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

## በዓለም ከ20 አመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ድል ላስመዘገቡት አትሌቶች የምስጋናና የማበረታቻ ሽልማት

በኮሎምቢያ ካሊ ከሐምሌ 25 እስከ ሐምሌ 30 ቀን 2014 ዓ.ም በተካሄደው የዓለም ከ20 አመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በ12 ሜዳሊያዎች ከአፍሪካ አንደኛ ከአለም ሶስተኛ ሆና በማጠናቀቅ እንደቀድሞው ስሟ ዘንድሮም በአትሌቶቿ በዓለም አደባባይ ከፍ ብላለች።

የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በኮሎምቢያ ካሊ በተካሄደው ከ20ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከዓለም ሶስተኛ ከአፍሪካ አንደኛ በመውጣት አመርቂ ድል ላስመዘገበው የአትሌቲክስ ልዑካን ቡድን የምስጋናና የማበረታቻ ሽልማት መርሐ ግብር በስካይ ላይት ሆቴል ማካሄዱ ይታወሳል።

በመርሐ ግብሩ ላይ የፌደሬሽን ምክር ቤት ዋና አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር በየዘመናቱ ድል ያስለመዳችሁን አትሌቶቻችን አሁንም አትሌቲክሱን በመምራት እያመጣችሁ ያለው ውጤት እጅግ ከፍተኛ ስለሆነ እንኮራባችኋለን በማለት አትሌቶቹን አመስግነዋል። በአሁኑ ሰዓት አለም አቀፍ ሚዲያ ኢትዮጵያ በአትሌቲክሱ ያገኘችውን አመርቂ ድል እና ሶስተኛውን ዙር የታላቁ ህዳሴ ግድብ የውኃ ሙሌት ብስራት ቀዳሚ ዜናቸው አድርገው እየዘገቡ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ክቡር አቶ ቀጀላ መርዳሳ፣ ባለፉት ዓመታት በቶኪዮ በነበረው ውድድር ስፖርቱ መዳከም የታየበት እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። በያዝነው ዓመት በሰርቢያ ቤልግሬድ የቤት ውስጥ ውድድር ብዙ ያልተነገሩ ድሎች የነበሩት ሲሆን ይህንንም ለማስታወስ ታላቋን አሜሪካን



አሸንፈው አትሌቶቻችን የአንደኛነት ድል ይዘው የመጡበት፣በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው 18ኛው የአለም ሻምፒዮና 10 ሜዳሊያዎችን ማግኘታችን አስታውሰው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና 12 መዳሊያ ይዘው ወደ አገራቸው በመምጣት ከፍተኛ ታሪክ የተመዘገበበት መሆኑን ተናግረዋል።

‹‹የዛሬ ድላችሁ የነገ ስንቃችሁ ነውና ጥረታችሁ ይቀጥል›› ሲሉም አሳስበዋል። አያይዘውም ታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በጉባ በርሃ 2ተኛ ዙር የሃይድሮ ፖወር ማመንጨት እና የሶስተኛ ዙር የውኃ ሙሌት በትጋት በመስራት ላይ ለሚገኙ ሠራተኞች ሁሉ ምስጋና አቅርበዋል።

ኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር አድርገዋል። የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አባላት፣ የአትሌቲክስ ልዑካን ቡድኑ አባላት እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል። ከልዑኩ ጋር ወደ ኮሎምቢያ ያቀኑ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አመራሮች፣ አሠልጣኞች እና የአትሌቲክስ ቡድኑ መሪዎች በየደረጃቸው የተለያዩ የገንዘብ ስጦታዎች ተበርክቶላቸዋል። ኢትዮጵያ በስድስት ወርቅ፣ በአምስት ብር እና አንድ ነሃስ ሜዳሊያ በአጠቃላይ በ12 ሜዳሊያዎች አሜሪካንና ጃማይካንም ተከትላ ነው በሶስተኛነት ያጠናቀቀችው።

የመንግስት ኮሙንኬሽን አገልግሎት ባወጣው መግለጫ፤ በኮሎምቢያ ካሊ ከተማ በተካሄደው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያ በወጣት አትሌቶቿ ከዓለም ሶስተኛ፣ ከአፍሪካ ደግሞ 1ኛ በመሆን አጠናቃለች። በውድድሩም በአዋቂ አትሌቶቻችን በ18ኛው የዓለም የትሌቲክስ ሻምፒዮና የተበሰረው የአሸናፊነት ገድል በወጣት ተተኪ አትሌቶቻችንም ተደግሟል። ድሉ የአሸናፊነት ስነ-ልቦና ትውልድ ተሻጋሪ የኢትዮጵያዊያን መለያ እሴት ስለመሆኑ ትልቅ ማሳያ ነው። ድል ማድረግ ብሎም ኢትዮጵያን በዓለም መድረክ ከፍ ማድረግ የአትሌቶቻችን መታወቂያ ነው።

በዚህ የአትሌቲክስ ሻምፒዮና ወጣት አትሌቶቻችን በአንድ ሰዓት ውስጥ ብቻ 5 የወርቅ ሜዳሊያ አሸንፈው ዓለምን አስደምመዋል። በውድድሩ በአጠቃላይ 6 ወርቅ፤ 5 የብር እና 1 የነሀስ ሜዳሊያዎችን ሰብስበዋል። ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም እምብዛም ውጤት አምጥታባቸው በማታውቀው የ1 ሺህ 500 እና 800 ሜትር እንዲሁም የመሰናክል ውድድሮች ሳይቀር የወርቅ ሜዳሊያዎች ተገኝተዋል። ይህም ኢትዮጵያ ያላትን የአትሌቲክስ እምቅ አቅም ከማሳየት አልፎ የአትሌቶቻቸችን የአሸናፊነት ስነልቦና የላቀ እንደሆነ ያመለክታል።

ወጣት አትሌቶቻችን ያስመዘገቡት ድል ኢትዮጵያ የአሸናፊዎች ሀገር መሆኗን ለዓለም ማህበረሰብ ያሳየ ነበር። ኢትዮጵያ የመቻል አቅሟ የት ድረስ እንደሆነ፤ ተተኪ ባለድል ትውልድ ያላት ጠንካራ ሀገር መሆኗንም ይጠቁማል። ኢትዮጵያ በፈተና ውስጥም ሆና ስኬትን የምታስመዘግብ፣ የማትሰበር ሀገር መሆኗን ወጣት አትሌቶቻችን ለአለም አሳይተዋል። ኢትዮጵያ በቀላሉ የማትሸነፍ፤ ህብረብሔራዊ አንድነት በየዕለቱ የሚያፀናት እና የሚያንፃት ሀገር እንደሆነች በኮሎምቢያ ካሊ ከተማ በተግባር ታይቷል።

Telegram https://t.me/ministry ofcultureandtourism
Facebook https://www.facebook.com/cultureandsportethiopia